


ለመስቀልህ እንሰግዳለን ፤
ትንሣኤህንም እናከብራለን ። (ያሬድ)

ክርስቶስ ተነሣ ከሙታን ፤
በታላቅ ኃይልና ሥልጣን ። (ያሬድ)

# ትንሣኤ




ክርስቶስ የእኛን ኃጢአት ለማስተሰረይ በእንጨት ላይ ተሰቀለ ።
(፩ኛ ጴጥ፡፪፡፳፬)



www.ethiopianorthodox.org

''ይህ መጽሔት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ሥርዓትና ዜና ፡ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ ''ትንሣኤ'' ተብሎ ተሰይሟል ፡፡

አዘጋጅ
ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ሐዋርያዊ ድርጅት
የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ
በወር አንድ ጊዜ
እየታተመ የሚወጣ ፡፡

የስልክ ቁጥር 116616
የመልእክት ሣ.ቁ. 3137
አዲስ አበባ

ማውጫ

| አርእስት | ገጽ |
| --- | --- |
| እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው አደረሳችሁ | ፩ |
| ሐክርስቶስ በእውነት ተንሥቷል | ፪ |
| የጸሎተ ሐሙስ ሥርዓተ ሕፅበት | ፬ |
| ደብዳቤዎች | ፯ |
| ለአባት የተላከ የደቅርታ ደብዳቤ | ፱ |
| የተሰቀለውን እንሰብካለን | ፲፩ |
| የሃይማኖት ዓምድ | ፲፪ |
| የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ዜና | ፲፫ |
| ቤተ ክርስቲያንና ቅርሶችዋ | ፲፬ |
| የጤና ዓምድ | ፲፭ |
| ሊቃውንቶቻችን | ፲፯ |
| መስቀሉና ሕይወታችን | ፲፱ |
| የሴቶች ዓምድ | ፳፫ |
| ምን እንርዳዎ ? | ፳፬ |
| ወጣቶች ጋብቻን ለምን ይፈራሉ ? | ፳፭ |
| መብት ከግዴታ ጋር | ፳፮ |
| የእመቤታችን ሥዕለ ቅርፅ | ፳፮ |
| የመጽሐፍ ቅዱስ ዓምድ | ፳፯ |

# እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው አደረሳችሁ

ክርስቶስ ተንሣ ከሙታን
በታላቅ ኃይልና ሥልጣን ፤
ሰይጣንን አሰረው ፤
አዳምን ነፃ አወጣው ፤
ሰላም !!
ከዛሬ ጀምሮ ይሁን ሰላም ።
ክርስቶስ ተንሣ ከሙታን
ሞትን ረገጠው ፤
በመቃብር ውስጥ ለአሉ ሕይወትንና የዘለዓለም ዕረፍትን ሰጣቸው ።

የምሥራቅ ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች በስሙነ ትንሣኤ "ክርስቶስ ከሙታን ተነሣ" በሚለው ቃል ሰላምታ ይለዋወጣሉ ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም ምሥራቃዊት እንደመሆንዋ መጠን ከሌሊተ ትንሣኤ ጀምሮ እስከ ሃምሳኛው ቀን ድረስ ከላይ የተጠቀሰውን ቃለ ሰላም ትጠቀምበታለች ። መዝሙርም አድርጋ ትዘምራዋለች ።

አዎ ቃሉ እውነተኛ ብሥራት ነው ። ትንሣኤ ፤ ኃይልና ሥልጣን ነፃነትና ሰላም ተበሥረውበታልና ።

እነሆ "ትንሣኤ" መጽሔት የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የትንሣኤ በዓል ምክንያት በማድረግ ለኢትዮጵያ ምእመናንና ምእመናት እንደሚከተለው መልካም ምኞቱን ይገልጣል ።

ምእመናንና ምእመናት ሆይ ክርስቶስ ፦ እንከዋን ለብርሃነ ትንሣኤው አደረሳችሁ ፤ ይህ ታላቅና መንፈሳዊ በዓል መድኃኒታችን ክርስቶስ በእውነት ከሙታን (ተለይቶ)እንደ ተነሣ የምትመሰክሩበት ፣ ለሙታነ መንፈስ ትንሣኤ መንፈስን የምትሰብኩበት ፣ ለሙታነ ሥጋ ትንሣኤ ሥጋ እንደአለ የምታስተምሩበት ፤ ኃይልና ሥልጣን ለአምላካችን ይሁን ብላችሁ አምልኮታችሁን የምትገልጡበት ፤ በቅኝ አገዛዝ ለአሉ አፍሪካውያን ወገኖቻችን ሁሉ ስለ ነፃነት ፤ በጦርነት ስለ አሉም ስለ ሰላም የምትጸልዩበት በዓል ይሁንላችሁ ።

ክርስቶስ ተነሥትዋል !
አዎ በእርግጥ ተነሥትዋል !

ያለ መከራና ሕማም
ያለ ችግርና ድካም
በደስታና በሰላም
ከርሞ እንደ ዛሬው
ያድርስን ያድርሳችሁ

ከ "ትንሣኤ" መጽሔት ድርጅት ክፍል ።



www.ethiopianorthodox.org

ርእሰ አንቀጽ

# ክርስቶስ በእውነት ተነሥቷል

የመነሣት ዓይነቱ ብዙ ነው ፤ ወድቆ መነሣት ፤ አንቀላፍቶ መንቃት ፤ ከተቀመጡበት ብድግ ማለት ትንሣኤ ሲባል ፤ አግኝቶ ማጣት ፤ ተዋርዶ መክበር ፤ ተሽሮ መሾም ወዘተ የመሳሰሉትም ሁሉ የትንሣኤን ተግባር የሚያመለክቱ ናቸው ።

እንዲሁም ክርስቶስ ሰው ሆኖ ሥጋን ለብሶ ያስተምርበት በነበረው ጊዜ የአራት ቀናት ሬሳ አልዓዛርን የዕለት ሬሳ ወለተ ኢያኢሮስን (የኢያኢሮስን ልጅ) አሥነሥቶ ነበር፤ይሁንእንጂእነዚህክርስቶስያስነሣቸውምቢሆኑ ሁለተኛ ሞተዋል አሁን ሁለተኛውንና የመጨረሻውን ትንሣኤ በመጠባበቅ ላይ ናቸው ።

የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ግን ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ሁሉ ግንኙነት የለውም ክርስቶስ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ ተሰቅሎ ሞቶ ፤ ተነሥቶ ለሰው ልጆች ሁሉ በጠቅላላ የነፍስ ነፃነታቸውን እንደሚያጐናጽፋቸው ቀደም ብሎ በነቢያት ተነግሮ ነበር ።

ይህንን የተነገረውን ቃለ ትንቢት ለመፈጸም ሲል ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ከድንግል ማርያም ተወለደ ፤ ይህንንም ሐዋርያው ጳውሎስ "የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ልጁን ላከ ከሴት የተወለደውን" በማለት ጠቅሶ ተናግሮታል ገላትያ 4 ፡ 4 ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም ከተወለደ በኋላ ከኃጢአት በስተቀር የሰው ልጆች የሚሠሩትን ሥራ ሁሉ እየሠራ ቀስ በቀስ አድጓል ፤ ለዘመዶቹ በመታዘዝ ፤ የወገኖቹን ባህልና ልማድ እያከበረ እንዳደገ ወንጌላዊው ሉቃስ ሲያስረዳ "ከእነርሱ ጋር ወደ ናዝሬት መጣ ፤ ለእነርሱም ይታዘዝ ነበር ። ኢየሱስም በጥበብና በቁመት ያድግ ነበር በጸጋም በእግዚአብሔር በሰውም ዘንድ" ይላል ሉቃስ 2 ፡ 40 ። 51 - 52 ።

ይሁን እንጂ ክርስቶስ ወደዓለም የመጣው በትዕዛዝ መተላለፍ የተነጠቀውን የሰው ልጆች ክብር መልሶ ዘለዓለማዊ ሕይወትን ለማጐናጸፍ ስለሆነ ይህንን ዓላማውን ከግቡ ለማድረስ አስፈላጊውን ነገር ሁሉ ከማከናወን ወደኋላ ያለበት ጊዜ የለም ። የሰው ልጅ ደኅንነት ሊሰጥ የሚችለው በራሱ መሥዋዕትነት መሆኑን አስቀድሞ ያውቀዋልና ልዩ ልዩ መከራን ከተቀበለ በኋላ ቅድስት ነፍሱን ከቅዱስ ሥጋው በገዛ ሥልጣኑ ለይቷል የዮሐንስ ወንጌል 19 ፡ 30 ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተሰቅሎ ፤ ሞቶ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ በመነሣት ዓለምን ከፍዳና ከመርገም እንደሚያድን ቀደም ብሎ የተነገረ ቢሆንም አንዳንድ ሰዎች የተነገረውን ትንቢት አላመኑም ነበር ፤ ካለማመናቸውም የተነሣ በክርስቶስ ላይ የሞት ፍርድ ፈርደው ፤ ሰቅለው ከገደሉት በኋላ ሥጋው ወደ መቃብር ከወረደ ጀምሮ መቃብሩን በፈረቃ የሚጠብቁ ጭፍሮችን መድበው መቃብሩን ነቅተው እንዲጠብቁ አድርገው ነበር ፤ ቢሆንም ጌታችን ክርስቶስ መቃብር ክፈቱልኝ ፤ መግነዝ ፍቱልኝ ፤ ደንጊያ ፈንቅሉልኝ ሳይል በዚያው በተስፋው መሠረት በሦስተኛው ቀን ተነሣ ፤ በተነሣም ጊዜ መቃብሩን ነቅተው እንዲጠብቁ በፈረቃ የተመደቡት ዘበኞች እየሰሙ እንደማይሰሙ ፤ እያዩ እንደማያዩ ሆኑ ።

በዚህ ጊዜ ቀደም ብሎ ክቡር ዳዊት "እግዚአብሔር ይነሣል ፤ ጠላቶቹም ይበተናሉ ፤ እግዚአብሔርም ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ተነሣ" በማለት የተናገረው ቃለ ትንቢት ፍጻሜውን አገኘ (መዝ.67 ፡ 1 ፤ 77 ፤ 65 እንዲሁም ሐዋርያው ጳውሎስ "ሞት በመሸነፍ ባሕር ተዋጠ ፤ ሞት ሆይ ! መውጊያህ የት አለ ? ሲኦል ሆይ ! ማሸነፍህስ የት ነው"? ብሎ እንደተናገረው በክርስቶስ ትንሣኤ የሞት ኃይሉ ደከመ ፤ ሥልጣኑም ተሻረ ፤ ተደመሰሰ ፤ ክርስቶስንም ይዞ ለማስቀረት አልቻለም 1ኛ ቆሮ 15 ፡ 54 ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ከርሠ መቃብር በወረደ በማግሥቱ እነ ማርያም መግደላዊት ሽቱን አዘጋጅተው የክርስቶስን አካል ለመቀባት ወደመቃብሩ ተጉዘዋል ፤ ከመቃብሩ እንደደረሱ ግን የክርስቶስን መቃብር እንደሚገባ ሆኖ አላገኙትም ፤ መቃብሩ ተከፍቶ በመቃብሩ ላይ የነበረው ደንጊያ ተፈንቅሎ ፤ በተፈነቀለው ደንጊያ ላይም ፤ አንድ ነጭ ልብስ የለበሰ መልአክ በማየታቸው በፍርሃትና በድንጋጤ ተዋጡ ፤

መልአኩም መፍራታቸውንና መደንገጣቸውን አውቆ አይዟችሁ ! አትፍሩ ! አትደንግጡ ! የተሰቀለውን ኢየሱስን እንደምትሹ አውቃለሁና ክርስቶስ አሁን ከዚህ የለም ተነሥቷል ፤ በማለት መልአኩ የክርስቶስን መነሣት በመጀመሪያ ለቅዱሳት አንስት አብሥሯቸዋል ።



መልአኩ ይህንን መልካም ወሬ (የምሥራች) ለቅዱሳት አንስት ያበሠራቸው በምሥጢር ጠብቀው እንዲይዙት ሳይሆን ባስቸኳይ ሂደው ለደቀ መዛሙርቱ እንዲናገሩ ጨምሮ አዝዟቸዋል ፤ እነርሱም እንደታዘዙት ሂደው የክርስቶስን መነሣት ለሐዋርያት ለማብሠር ችለዋል ።

ክርስቶስ ስለእኛ በደልና ኃጢአት ተሰቅሎ ሞቶ ተነሥቶ ከፍዳና ከመርገም ነፃ አድርጐናል ከእንግዲህ ወዲህ ግን እኛ ከሕግ ወጥተን ብንበድል ክርስቶስ ሁለተኛ ስለእኛ ኃጢአትና በደል አይሞትልንም ፤ በዕርግጥ ክርስቶስ ሁለተኛ ወደዚህ ዓለም ይመጣል ፤ ግን የሚመጣው ስለ ኃጢአታችን ሁለተኛ ለመሞት ሳይሆን አዝክሮተ ፍቅር ለጻድቃን አዘክሮተ በቀል ለኃጥአን ለማድረግ ነው ።

እኛ ክርስቲያኖች የክርስቶስ ተከታዮች እንደመሆናችን መጠን ስለ ክርስቶስ መከራና ሥቃይ መሞትና መነሣት እንዲሁም ስላደረገልን ቸርነት የመመስከር ግዴታ አለብን ለምንሰጠውም ምስክርነት ልዩ ልዩ ምክንያት መስጠት አይገባንም ሐዋርያው ጳውሎስ "ለነፃነታችሁ ምክንያት አትስጡ" ይላል ክርስቶስ ብዙ ፀዋትወ መከራን ተቀብሎ ሞቶ ተነሥቶ በትንሣኤው ያጐናጸፈንን ነፃነት በማይገባ ምክንያት ከእኛ እንዲነጠቅ ማድረግ አይገባንም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠን ነፃነት ለሁልጊዜ ከእኛ ጋር እንዲኖር ክርስቶስ በእውነት ተነሥቷል እያልን መናገር ፤ መመስከር ፤ ማስተማር ክርስቲያናዊ ግዴታችን ነው ፤ ለዚህም መንፈሳዊ ተግባር ወንድ ሴት ትንሽ ትልቅ አያሰኝምና ሁላችንም በኅብረት "ክርስቶስ ተነሥቷል" የሚለውን የምሥራች ቃል ሳልሰሙት እናሰማ ።



www.ethiopianorthodox.org

# የጸሎተ ሐሙስ ሥርዐተ ሕፅበት

ከስቅለት ዐርብ በፊት የሚውለው ሐሙስ በክርስቲያኖች ዓለም በተለያየ ስም ይጠራል ። ለምሳሌ ሀ ጸሎተ ሐሙስ ይባላል ፡- ይህም መድኃኒታችን ክርስቶስ ሐዲስ ሥርዐተ ቊርባንን በሠራበት ጊዜ የጸለየውን ጸሎት ያስታውሳል ። ይህ ብቻ አይደለም ፤ ከሥርዐተ ቊርባን በኋላ ሊገድሉት በሚፈልጉት ሰዎች እጅ ከመያዙ በፊት በጌቴ




ክርስቶስ ስለ ክፉ አድራጊዎች በጌቴ ሴማኒ ጸለየ



ሴማኒ ውስጥ የጸለየውንም ጸሎት ያመለክታል ፤ በጌቴሴማኒ የጸለየው ሐሙስ ለዐርብ አጥቢያ ነውና ።

ለ የነፃነት ሐሙስ (ሺ.ርተርስዴይ ) በመባል ይጠራል።ይህ ስያሜ ክርስቶስ በዕለተ ሐሙስ ሥርዐተ ቊርባንን በሰየመበት ወቅት ሥጋው በመስቀል



ክርስቶስ በጸሎተ ሐሙስ ማታ ሥርዐተ ቊርባንን ለደቀ መዛሙርቱ አሳየ ።

ላይ ስለ ኃጢአት ይቅርታ እንደሚቆረስ ደሙም በመስቀል ላይ ስለ ብዙኃን ደኅንነት እንደሚፈስ የተናገረውን ቃል ያመለክታል ። ከዚህም ሌላ በእርሱ የሚያምኑ ሁሉ ከኃጢአት ባርነት ነፃነት እንደሚያገኙ የሚያመለክተው የፋሲካ በግ ተሠውቶ ክርስቶስና ደቀ መዝሙርቱ የነፃነትን በዐል ለመጨረሻ ጊዜ በአንድነት አክብረዋልና በዚሀ ምክንያት የነፃነት ሐሙስ ተብሎ አል ።

ሐ ምንዲ ሐሙስ ይባላል ፤ ይህም ትእዛዘ ሐሙስ ማለት እንደሆነ በቃሉ የሚጠቀሙ ክርስቲያኖች ይናገራሉ ፤ በዕለተ ሐሙስ ሐዲስ ትእዛዝና ሐዲስ ሥርዐት መስጠቱን ያሳስባል ። ሐዲስ ሥርዓትና ሐዲስ ትእዛዝ የምንለው ፡- ሥርዐተ ኦሪት ተለውጦ ሥርዐተ ወንጌል መተካቱን ፤ በትእዛዘ ኦሪት ምትክ ትእዛዘ ወንጌል መታወጁን ለመግለጥ ነው ። ይህም ሁሉ የሆነ በጸሎተ ሐሙስ ዕለት ነው ። በተጨማሪም ምንዲ የሚለው ቃል በእንግሊዝኛ (ሞኒ) ገንዘብ የሚለውን ቃል ስለሚጠጋ የስጦታ ቀን ማለት እንደሆነ የሚተረጉሙት አሉ ። ከዚህም የተነሣ የምዕራብ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን በጸሎተ ሐሙስ ዕለት ገንዘብ አበባና ሌላም ልዩ ልዩ ስጦታ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይወስዳሉ። ይህ ተግባር ክርስቶስ ኅብስቱን አንሥቶ "ይህ ሥጋዬ ነው እንኩ ብሉ ፤ ይህ ደሜ ነው እንኩ ጠጡ" በማለት በጸሎተ ሐሙስ የፈጸመውን ድርጊት በግልጥ ያሳያል ።

መ ፔድላቪዩም ፡- ሕፅበተ ሐሙስ ማለት ነው ይህ ደግሞ መድኃኒታችን ክርስቶስ ከእራት በኋላ የደቀ መዛሙርቱን እግሮች ማጠቡን ለማስታወስ የተሰጠ ስያሜ ነው ። ክርስቶስ በዚህ ዓለም በኖረበት ጊዜ የፈጸማቸው ድርጊቶች ሁሉ በቤተ ክርስቲያን በተለያየ መልክ ሲታወሱ ይኖራሉ ። በተለይ በዚህ ጽሑፋችን በጸሎተ ሐሙስ ዕለት የተፈጸመው ሥርዐተ ሕፅበት በዓለም ባሉት ቤተ ክርስቲያን ምን ዓይነት ትርጓሜና መታሰቢያ እንዳለው እንገልጣለን ።

1ኛ/ አብዛኛዎች የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት በጸሎተ ሐሙስ ዕለት ሊቀ ካህናቱ ወይም ጳጳሱ በቤተ ክርስቲ



www.ethiopianorthodox.org



ጌታችን ኢየሱስ ከእራት በኋላ የደቀ መዛሙርቱን እግር በማጠብ ትሕትናን አስተማረ


ያን የተገኙ የምእመናንን እግር በውኃና በወይን ቅጠል ያጥባል በኢትዮጵያ ኦ. ተ.ቤ. ክርስቲያንም ከዚህ ያልተለየ ሥርዐት ይፈጸማል ።

2ኛ በላቲን ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳሱ (ፓፓው) የዐሥራ ሁለት ክርስቲያኖችን እግሮች ብቻ ያጥባል ከማጠቡም በፊት ከዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ዐሥራ ሦስት 1 - 20 ያነብባል ።

ይህ ሥርዐት በቀጥታ ፊደል በፊደል ክርስቶስ የደቀ መዛሙርቱን እግር እንደ አጠበ ለማሳየት ያህል ነው ።

3ኛ/ በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ በዚሁ በጸሎተ ሐሙስ ዕለት ሊቀ ካህናቱ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን ንዋያተ ቅዱሳት ያጥባል ፤ ለምሳሌ ፦ መሠውያውን ፤ ዕዋዎችን የቤተክርስቲያኑን ወለልና ግድግዳ እንዲሁም ሊታጠቡ የሚችሉ አልባሳትን ሁሉ ያጥባል ። በግልጥ አነጋገር ቤተ ክርስቲያኑን ያጸዳል ። ስለዚህም ጸሎተ ሐሙስን እንደ ዝግጅት ቀን ይቆጥሩታል ። የትንሣኤን በዐል በደመቀ ሥነ ሥርዐት ለማክበር ከዚያ በፊት ሐሙስ ሁሉን ነገር ያጸዳሉ በአጠቃላይ አስተሳሰብ ፦ ክርስቶስ የደቀ መዛሙርቱን እግሮች ማጠቡ ቤተ ክርስቲያንን ከኃጢአት እንደ አነጻት ማመልከቱ ነው ብለው ይተረጉማሉ ። ይህ አይነት ሥርዓት በተለይ በአስጳንያ (ስፔይን) ቤተ ክርስቲያን እስካሁን ይታያል ። የተጀመረውም በ588 ዓ.ም. ነበር ። በዐሥረኛው ምእት ዓመት ደግሞ በሮም ቤተ ክርስቲያን ተለመደ ።





የክርስቶስን አርአያ በመከተል የኦርቶዶክስ ቤ ክርስቲያን መሪ እግር ሲያጥብ

4ኛ አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ሥርዐተ ሕፅበትን በተለየ በተራ ምሳሌ ያሳያሉ ። ይኸውም ካህኑ የእራት ግብር ያዘጋጃል ፤ የተጋባዦችን እጅ ያስታጥባል የምግብ ማቅረቢያ ዕቃዎችንም ሁሉ ያጥባል ይወለውላልም ። እንግዲህ ይህ ሁሉ አስተሳሰብ ክርስቶስ በትሕትና ለፈጸመው ድርጊት በተጨባጭ ሁኔታ መታሰቢያ ለማድረግ መሆኑንማንም ክርስቲያን ይረዳዋል ። ግን ለመታሰቢያነቱ የሚስማማ ትክክለኛው ሲምቦል (አምሳል) የትኛው ነው? ቢባል ይህ ልክ ነው ፤ ያኛው ልክ አይደለም ማለት የሚቻል አይመስልም።

ምክንያቱም ሁሉም የክርስተቶስን ትሕትና አምነው መታሰቢያውን በልዩ ልዩ መልክ ለመግለጥ ሞክረዋልና ።

በጸሎተ ሐሙስ ከእራት በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የደቀ መዛሙርቱን

እግር ለምን አጠበ ?

1ኛ ይህን ተግባር ደቀመዛሙርት ራሳቸው ማድረግ ሲገባቸው አላደረጉምና በእነርሱ ፋንታ የእነርሱን ሥራ ለመሥራት ነው ። 2ኛ መልካም ምሳሌ ለመሆን ነው ፤ መምህርና ጌታ ሲሆን ይህን ታላቅ ትሕትና መፈጸሙ ለደቀ መዛሙርቱ ዐቢይ ትምህርት ይሆናቸዋልና ። 3ኛ ክርስቶስ በዚያ ዘመን የነበረው ኅብረተሰብ የሚያደርገውን



www.ethiopianorthodox.org

# ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

የ12ኛ ክፍል ተማሪ ነኝ ። ከዚህም ጋር የኦርቶዶክስ ቤ/ክርስቲያን ዲያቆን ነኝ ። 12ኛ ክፍልን እንደጨረስሁ ቴዎሎጂ (ነገረ መለኮት) ለመማር እፈልጋለሁ ። ግን የኢትዮጵያ ኦ.ተ. ቤ/ክርስቲያን መንፈሳዊ ኮሌጅ የላትም ስለዚህ መንፈሳዊ ፍላጎቴን እንዴት ማሟላት እችላለሁ ?

ዲያቆን ተፈራ ገሠሠ
አ.አ.

● ዲያቆን ተፈራ ፣ ለጥያቄህ በቂ መልስ ለማግኘት ከአ.ቤ. ባለሥልጣናት አንዳንዶችን አነጋገረን ነበር ። የስጡንም መልስ እንዲህ ነው ለጊዜው መንፈሳዊ ኮሌጅ የለንም ። ግን በግሪክና በራሺያ ቤ/ክርስቲያን በኩል ነፃ ስኮላርሽፕ ስለሚኖር ተራውን ቢጠብቅ ወደዚያ ሄዶ ቴዎሎጂ መማር ይችላል ። ከዚህ ላይ አንድ ነገር ልነግርህ እወዳለሁ የግሪክና የራሽያ ቤተክርስቲያን ለክርስቶስ ሁለት ባሕርያቶች እንደአሉት ታምናለች ሌላም ብዙ ልዩነቶች ይኖራሉ። እንግዲህ ነገሩን ለስኮላርሽፕ ክፍል ደጅ ጠኚ ማመልከቻ ብትጽፍ መልካም ዕድል እንደሚኖርህ እገምታለሁ ። ካልቻኮልህም ቤተ ክርስቲያናችን መንፈሳዊ ኮሌጅ እንዲከፈት ጥናት በማድረግ ላይ ናት ።

★ ★ ★

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

እኔ የኦርቶዶክስ ተ. ሃይማኖት አማኝ ነኝ ልጅ ወዳጄም እንደ እኔ ክርስቲያን ነው ቤተሰቦቻችንም ክርስቲያኖች ናቸው እኔና ልጅ ወዳጄ ከተዋወቅን ቆይተናል ። እስካሁን በሃሳብ አንድ ነን ፣ በመከባበርም እንኖራለን ። በአንድነት ወደ ቤተክርስቲያን እንሄዳለን ። ግን ሰዎች ያሽሟጥጡናል ። ሆኖም እኛ ለሐሜቱ ቦታ አንሰጠውም ። በእንደዚህ ያለ ሁኔታ ስንኖር አሁን ልጅ ወዳጄ ወደ ቤ/ክርስቲያን መሄድን አቋረጠ ። ለምን እንደአቋረጠ ብጠይቀው "እኔ የትም ሆኜ ብለምነው እግዚአብሔር ይሰማኛል" አለኝ ። እርግጥ እግዚአብሔርን ከዶአል ማለቴ አይደለም ፤ ግን የቤ/ክርስቲያንን ሥርዓት ሳያከብሩ እግዚአብሔርን እምናለሁ ማለት ይቻላልን? ደግሞስ በማቴ. 7 20-22 እንደ ተጻፈው "በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ ፣ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም" ያለው ቃል ሊመለከተው አይችልምን

ወ/ት ደብረ ወርቅ ግዛው
ከይርጋ ዓለም

● ወይዘሪት ደብረወርቅ ከሁሉ በፊት ስለ መልካም ጥያቄሽ እናመሰግንሻለን ።

"እሱ" በማለት የገለጥሽውን ግለሰብ ልጅ ወዳጅ ብለነዋል ። እርግጥ ነገሩ ገብቶናል ። ክርስቲያንነት በቤት ተቀምጦ እግዚአብሔርን እምናለሁ ማለት ብቻ አይደለም ። ሥርዓቱንም መከተል ያስፈልጋል ። ወደ ቤ/ክርስቲያን መሄድ ፣ ቃሉን መስማትና ማሰማት ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር መተዋወቅ የሚፈለገውንም እስተዋጽኦ ማድረግ ይገባል ። ወ/ት ደብረ ወርቅ ለ... የሚከተለውን ጥቅስ አንብቢለት" .... ለፍቅርና ለመልካም ሥራ እንድንነቃቃ እርስ በርሳችን እንተያይ ፣ በአንዳንዶቹም ዘንድ ልማድ እንደሆነው መሰብሰባችንን አንተው እርስ በርሳችን እንመካከር እንጂ ዕብ. 10 24-25 ።

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በአሁኑ ጊዜ የአዲስ አበባ አብያተ ክርስቲያናት አስተዳዳሪዎች በብዛት መነኮሳት ናቸው የቀሳውስት አስተዳዳሪዎች እጅግ ጥቂቶች ናቸው ። ይህ ሊሆን የቻለው ሀ/ መነኮሳት ከቀሳውስት በመዓርግ ይበልጣሉን ? ለ/ በችሎታ ብልጫ ስለአሳዩ ነውን ? ሐ/ በጠቅላላ ለመነኮሳት ልዩ ክብር የተሰጠበትን ምክንያት ቢገልጡልኝ?

ፍስሃ ዘለዓለም
ከአዲስ አበባ

● አቶ ፍሥሃ ዘለዓለም ጥሩ ጥያቄ አቅርበዋልና ከምስጋና ጋር ተቀብለነዋል ። በእውነት ከቀሳውስት መነኮሳት በመዓርግ ይበልጣሉ ለማለት የሚደፍር የለም ። እኛም ይበልጣሉ አንልም ። በችሎታም ቢሆን እንደ እእምሮአቸውና ንቃተ ሕሊናቸው እንጂ ምንኩስና የችሎታ ምልክት አይደለም ። ነገር ግን በዋናው ከተማ በአዲስ አበባ አብያተ ክርስቲያናት የመነኮሳት አስተዳዳሪዎች መብዛታቸው የምንኩስናን ሥርዓት ባለማወቃቸው ይመስለናል ። መነኩሴ በገዳም እንጂ በከተማ እንዲኖር መጽሐፉ አይፈቅደውምና ። እርግጥ በከተማ እንዲኖሩ የሚፈለጉ መነኮሳት እሉ እነዚህም ርእሰ ቤተክርስቲያኑና የሲኖዶስ አባላት ናቸው ።

★★★

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በቅድሚያ ሁሉን በሚችልና ለዘለዓለም ሕያው ሆና በሚኖረው በእግዚአብሔር ስም የከበረ ሰላምታዬን አቀርባለሁ ።

ከዚህ ቀደም በፖስታ መልእክት የግእዝ ቋንቋ ትምህርት ይሰጥ ነበር ። ነገር ግን ለሌላው ዝግጅታችሁ የተፋጠነ መሻሻል ሲታይ ለዚህ ለቤተ ክርስቲያንዋ መደበኛና አኩሪ ለሆነው ቋንቋ መስፋፋት ጉዳይ ቸል በማለታችሁ ቅሬታ ተሰምቶኛልና ትምህርቱ ወደፊት በምን ዓይነት መንገድ እንደሚሰጥ መፍትሔ ቢፈለግለት መልካም ነው እላለሁ ።

ደምሴ በቀለ
ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የደቡብ
ክ/ሀ/ቅ/ን/ባንኮች ጽ/ቤት አዋሳ

● አቶ ደምሴ በቀለ ብዙ ሰዎች የተባበሩበትን ጥያቄ እርስዎም በመጠየቅዎ እናመሰግንዎታለን ። እውነት ነው ግእዛችን ለቤተ ክርስቲያናችን መደበኛ ቋንቋ ነው ። ዛሬም ቢሆን በብሔራዊ ደረጃ ለአዳዲስ ተርምኖሎጂዎች በጣም ጠቃሚ ሆናአል ። ለምሳሌ "አብዮት ግብታዊ መርሐ-ብሔር .....ወዘተርፈ" ። ስለዚሁ ጉዳይ ብዙሃን ሕዝብ ስለጠየቁን በመጽሔታችን ውስጥ አንድ የግእዝ ዓምድ ከፍተን ለማስተማር በጥናት ላይ ነን ። ጥናቱ እንደአበቃ ይታተማል እስከዚያው አቶ ደምሴ ጸጋ እግዚአብሔር የሀሉ ምስሌከ ወምስለ ኩሉ ሰብእ ቤትከ ።

መልካም ልማድ ሁሉ ያደርግ ነበር ። ለምሳሌ ፦ በጥንቱ በአይሁድ ኅብረተሰብ ዘንድ እንግዳን መቀበልና መጋበዝ ፤ ከግብዣውም በኋላ ወይም በፊት የእንግዳውን እግሮች ማጠብ በጣም የተለመደ ነበር ፤ ያው ግን ደግነትና ትሕትና ሆኖ ይቆጠር እንደ ነበር ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳል ። ስለዚህም የሚከተሉትን ጥቅሶች ማንበብ በላይ የገለጥነውን ሀሳብ ለማስተዋል እንደሚረዳ እንገምታለን (ዘፍጥ 18 ፤ 4 ፤ 24 ፤ 32 ፤ መሳፍ 19 ፣ 21 ፤ 1 ጢሞ 5. 10) ።

በመጨረሻ ይህን ጽሑፍ እንዲህ እናጠቃልላለን ፣ ክርስቶስ እንደሠራ መሥራት አንችልም ። ሆኖም የሠራውን ሁሉ ለእኛ በሚረዳን መንገድ መግለጥ እንችላለን የሠራውን መታሰቢያ ሁሉ ለትውልደ ትውልድ ማቆየት ለክርስቲያኖች ተቀዳሚ ተግባር መሆኑን የቀደሙን አስተማሩን።እኛም ለሚከተሉት እናስተምራለን።ዛሬ የእንግዶችን እግሮች ተንበርክኮ ለማጠብ ጊዜው አይፈቅድ ይሆናል፤ምክንያቱም እግርን ብቻ ሳይሆን አካልን በሙሉ ለመታጠብ የሚያስችል መታጠቢያ ቤት ተዘጋጅቶአልና ። ስለዚህ ክርስቶስ እግር በማጠብ የፈጸመውን ምግባረ ትሕትና በማናቸውም መልካም ሥራ መግለጥ እንደሚቻል እንማራለን ለሌሎችም እናስተምራለን ።

ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ



# ለአባት የተላከ የይቅርታ ደብዳቤ

ውድ አባቴ ሆይ እኔ ልጅህ ቅድስት ግዛው ነኝ አባቴ ሆይ አንተና እናታችን በእግዚአብሔር እርዳታና ጠባቂነት እኛን የመሰለ ፍሬዎችን አግኝታችኋል ሆኖም እስከቅርብ ጊዜ ድረስ እንደልጅነታችን ሳናስደስትህ መኖራችን ግልፅ ነው ።

ውድ አባቴ ሆይ አሁንም የምነግርህና የምስምንህ ነገር አለኝ ይኸውም ከዚህ በፊት በሰይጣን አሳሳችነት ካንተ ቃል ወጥቼ የእግዚአብሔርን መንገድ ረስቼ ስወናበድ ቆይቻለሁ ። ይህ ሁሉ ግን አሁን ገና ገባኝ ስህተቴንም በማሰብ በጣሙን እዘንኩ ወደ እምላኬም አለቀስሁ ጸለይሁ እግዚአብሔር እምላክም ይቅር ባይ እንደመሆኑ መጠን ጥፋቴንና ስህተቴን ሳይመለከት ይቅር ብሎኝ ይኸው ከብዙ መከራ አውጥቶኛል ።

አንተም አባቴ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነህና የእግዚአብሔርንም ቃል ተቀባይ ነህና እግዚአብሔር አምላክ "ይቅር ብትሉ የሰማይ አባታችሁ ይቅር ይላችኋል" ያለውን አስታውሰህ "እንደጠፋው ልጅ ገንዘቡን አባክና ወደሩቅ አገር ሄዶ ገንዘቡንም በጨረሰና በተቸገረ ጊዜም ወደ አባቱ ተመልሶ አባቴ ሆይ ይቅር በለኝ ብሎ አባቱን እንደለመነውና አባቱም በደስታ እንደተቀበለው ሁሉ እኔም ከቃልህ ወጥቼ ጥፋቴ ብዙ ችግርንና መከራን ባደረሰብኝ ጊዜ ወዳንተ መጥቼ ይቅርታ የምለምንህ ልጅህን ይቅር ብለህ በአዲስ ልብ ትቀበለኝ ዘንድ እለምንሃለሁ ።

ከዚህም በመቀጠል ልነግርህ የምፈልገው ነገር አለ ይህንንም እንደአባትነትህ በትክክል አዳምጠኸኝ እንድታመዛዝነው እለምንሃለሁ ።

አባቴ ሆይ እኔና እናቴ ይኸው ሁልጊዜ እንደምታየው ምንም ስምምነት የለንም እንደ እናትና ልጅ መተያየታችን ቀርቶ እንደጠላት እንተያያለን ይኸንንም ለአንተ ላባቴ ብቻ ሁልጊዜ እንደምነግርህ አንተም አባታዊ ምክርህ ተለይቶኝ አያውቅም ነገር ግን አንተ እንደምትመክረኝ እስካሁን በትእግሥት ችያለሁ አሁን ግን ፍጹም መታገስ ስላቃተኝ ይኸንን ልጽፍልኽ ተገድጃለሁ አባቴ ሆይ እኔ ያለአንተ በስተቀር በቤት ውስጥ ወንድም እያለኝ እንደሌለኝ እናት እያለችኝ እንደሌለችኝ ሆኜ እግዚአብሔርንና አንተን ብቻ ተስፋ በማድረግ የምኖር ነኝ ።

አንተም እንደምትመክረኝ ሁሉ ጓደኛ እንዳያበላሸኝ ስለምትመክረኝ ያንተንም ቃል በመቀበል ለመፈጸም ጓደኛ የለኝም እህቴም ገና ያልደረሰች ክፉውንና ደጉን የማታውቅ እኔ እሷን መምከር እንጂ እሷ እኔን ለመምከር ምስጢሬን ለመካፈል ያልበቃች በመሆኗና ካንተ ለኔ አሳቢ ስለሌለኝ ይህንን ጉዳይ ላንተ ባስረዳህ መፍትሔ ታገኝለታለህ በማለት ላማክርህ፣አንተም ሰዎች የሚሉትን ሳትቀበል አይተህ እመዛዝነህ የምትለውን ለመስማት ነው ።

በእርግጥ ይህ ነገር አዲስ ሊሆንብን አይገባም በወንጌልም ተጽፏልና "በምድር ላይ ሰላም ልሰጥ የመጣሁ አይምሰላችሁ መለያየትን እንጂ አባት በልጁ ፣ ልጁም በአባቱ ላይ እናትም በልጅዋ ልጅም በናትዋ ላይ ተነሣስተው ይለያያሉ" በወንጌል የተጻፈው ሁሉ ሊፈጸም ግድ ነውና ይህ አዲስ አይሆንብንም እያስደንቀንም ነገር ግን ይህ ትንቢት በኛ እንዳይፈጸም ለሰይጣን መግቢያ ቀዳዳ እንደማጥፋት ፋንታ እኛው እራሳችንን ለጠላታችን በር ስንከፍት በእውነቱ ሊያስገርም ይገባል ሊያሳዝንም ይችላል፤

"ልጆቼ ሆይ ለወላጆቻችሁ በእግዚአብሔር ታዘዙ ይህ የሚገባ ነውና እናንተ ወላጆችም ልጆቻችሁን በጌታ ምክር በተግሣጽ አሳድጓቸው እንጂ አታስቆጧቸው" የሚለውን ቃል ምናልባት እሷ መሐይምን ስለሆነች አንብባ መረዳት አትችል ይሆናል ይኸንንም አንብበን ተረድተን ለማያውቁት ማስረዳት የኛ ፋንታ ነበር እስዋ ግን እንኳን ይኸንን ቀርቶ የራሷን ስህተት በምንነግራት ጊዜ ተቆጥታ ታኮርፋለች ። በእርግጥ ከትላልቆች በስተቀር ልጆች አያውቁም ማለት አይደለም እሷ ግን እንደዚያ ይመስላታል ይኸንንም በአይንህ ያየኸው ነው፤

እንግዲህ ውድ አባቴ ሆይ ይህን ነገር ማለት

# ይህን ያውቁ ኖሯል ?



ይህን ያውቁ ኖሯልን ? ለተሰኘው ዐምዳችን አስደናቂ ታሪኮችን የሚያቀርቡልን አቶ እጅጉ ረታ እኚህ ናቸው ።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በ19ኛውና በ20ኛው ምዕት ዓመት የተገለጠችባቸውን ቦታዎችና ጊዜዎች ከምላ ጉደል ሚራክል ኦፍ ጎድ ከተባለ ከአንድ የውጭ ሀገር መጽሐፍ ተርጉሜ በቁጥር 15 እና 17 ትንሣኤ መጽሔት እትሞች ማቅረቤ ይታወሳል ። ታዲያ ይህ አሁን የማቀርበውም ካለፉት እትሞች በይቀጥላል የቆየውን ነው ። እዚህ ላይ ሳልገልጥ የማላልፈው ነገር ቢኖር እንዳለፈው ጊዜ ሁሉ የእመቤታችንን መገለጥ ብቻ በማቅረብ አለመወሰኔን ነው ። መላእክትና ይልቁንም የዓለም መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ ለአንዳንድ ወዳጆቹ የተገለጠበት ጊዜ መኖሩን በዚሁ መጽሐፍ ተጽፎ ስላገኘሁ ሳልፈው አልፈለግሁም ። ይህንንም በተጨማሪ አቅርቤአለሁ ። 1/ በ1219 ዓ.ም. በፈረንሳይ ሀገር አርሊያንስ በተባለች መንደር ለምትኖር ዲን ረጅናል ለተባለች ወይዘሮ ሁለት ውብ የሆኑ ደናግል አስከትላ እመቤታችን ተገልጣ ታይታለች ።

2/ በ1277 ዓ.ም. በኢጣልያ ሀገር ቶሌን ቲኖ በምትባል መንደር ባለች አንዲት ቤተ ክርስቲያን ከመንበረ ምሥዋዕ በላይ ከፍ ብሎ አንድ ብሩህ ኮከብ ቅድስት ኒኮላስ ለተባለች ሴት ታይቷታል ። እንዲሁም በዚሁ ምሥዋዕ ዙርያ ቆመው መላእክት ተገልጠውላታል ።

3/ በ1288 ዓ.ም. በኢጣልያ ሀገር ፎሊኞ በምትባል መንደር ቅድስት አንጂሊና ለተባለች ሴት መድኃኒታችን ብዙ ጊዜ እየደጋገመ በመገለጥ በመስቀል ላይ የደሙትን ቁስሎቹን አሳይቷታል ።

4/ እመቤታችን ድንግል ማርያምና ልጅዋ መድኃኒታችን ክርስቶስ ለቅድስት ሊድዊና በሆላንድ ሀገር ሺዳም በተባለች ቦታ በ1413 ዓ.ም. ተገልጠውታይተዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

ነገሩ ባንተ ያምር ይሆናልና እናታችንን በት ርፍ ጊዜዋ አንዳንድ የመጻሕፍ ቅዱስ ትምህርቶችን በመስጠት ከዚህ ከስህተቷ አድናት። በስም ክርስቲያን መባል ብቻ ምንም እንደማይጠቅም አንተም ታውቀዋለህ ካንተ መቸም እኔ አውቃለሁ ማለቴ አይደለም ይሄንን ደግሞ እግዚአብሔርም ይላልና "በሰማይ ያለውን ያባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያትን የሚወርስ አይደለም" የሚለውንም ማስታወስ ይኖርብናል ።

በእርግጥም እኔ እናቴን በብዙ ዓይነት መንገድ ላስረዳት ፈልጌ ነበር ነገር ግን አልቻልኩም እኔ የኔንና የሷን ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርስ ምን ይለናል ። ሰውስ በማን ያያል በማለትም አስባለሁ በእውነት አባቴ ሆይ አንተም ሆንክ ሌሎቹ እንደሚሉኝ ለእናቴ እኔ በሥራ ማገዝ አቅቶኝ አይደለም እንኳን ለሷ በየጓደኞቻችን ቤት ሥራ በሚኖር ጊዜ ምንም ሳልደክም የምሠራ መሆኔን ታውቃለህ ፣ እሷም ከቤት ስትወጣ የምሠራውን ሥራ ታያለህ እሷ እያለች ግን ገና በማድ ቤት ስገባ ትንሽ ነገር ፈልጋ ቀኑን ሙሉ ስትሳደብ ስትራገም ትውላለች ይህንንም አንተም ሆንክ የቤት ሠራተኞች የሚያውቁት ስለሆነ ይህ ዓይነት ጥያቄ በእርግጥ ከውጭ ለሚመጡ ሰዎች መጠየቅ የሚገባው ነው ። ነገር ግን ምን ብዬ ልመልስ? የሆዴንስ ብነግራቸውማን ያምነኛል? በማለት ልቤ ይጨነቃል መልኤ እኔ ሰው የፈለገውን ቢለኝ ምን ችግረኝ እንኳን እኔ አንድ ቅንጣት ቅቅርና እግዚአብሔር እንኳ ታምቶ የለምን እግዚአብሔር ሁላችንንም እንደየሥራችን ያውቀናል ነገር ግን እንደየጥፋታችን አይመልከትብን እሱ ምሕረትን ሰላምን ይስጠን በማለት ልቤን አረጋጋዋለሁ ።

አሁንም አንባቢዎቻችንና ውድ አባቴን የምለምነው ሰላምን ያወርድልን ዘንድ ተግታችሁ ከልባችሁ ጸልዩልን ።

ወንድሜም የአልኮል ሱሰኛ ከሆነ ቆይቷል እኔም ሆንኩ አባቴ ይህን እንዲተው ብንመከረው አልሰማ ብሏል እንዲያውም እኔን ስንኳ ለምን ታሚኛለሽ በማለት ቀን ከሌሊት ይጣላኛል እኔም ወደ እግዚአብሔር በመጸለይ የሚለውን ሁሉ ባልቀበለውም እሰማዋለሁ አባቴም ስለሱ ሆነ ስለሁላችን ከመጸለይ ወደኋላ አትስለሱ ሆነ ስለሁላችን ከመጸለይ ወደኋላ አትበል ትልቅ ዛፍ ከስሩ ላሉት ለትንንሽ እፀዋቶች ጥላ እንደሚሆናቸው ሁሉ አንተም አባታችንለኛ ያለኸን አንተ ብቻ ስለሆንክ ከምክርህ ከጸሎትህ ከተግሳጽህ አትቆጠብብን ።

በኔም ያየህብኝ ጥፋት ካለ እንድትመክረኝና እንድትገስፀኝ አባታዊ ምክርህም እንዳይለየኝ በይቅርታ እለምንሃለሁ ።

ልጅህ ወ ት ቅድስት ግዛው

---

5 በ1424 ዓ.ም. በፈረንሣይ ሀገር ዶምርሚይ በተባለች ቦታ ዣን ዳርክ ለተባለች ብላቴና ሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤልና ሌሎችም ቅዱሳን ተገልጠው ታይተዋታል ።

6/ ከ2/3/1440 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ዕድሜዋ ፍጻሜ ድረስ ማለት ለሐያ ሦስት ዓመታት ቅድስት ፍራንሲስ የተባለች ሮማዊት ጠባቂ መልአኳን በገሐድ ታየው ነበር ይባላል ።

7/ በ1463 ዓ.ም. ቦሎኛ ፣ በኢጣልያ ሀገር ነዋሪ ለሆነች ለቅድስት ካቴሪና ጌታ በመንበረ ክብሩ እንዳለ ሆኖ ተገልጦ ታይቷል ።

8/ በ10/8/ 1519 ዓ.ም በፈረንሳይ ሀገር ሞንት ቫርጲይ በተባለ ኩረብታ በላይ ከፍ ብላ ቆማ እመቤታችን ገሮንጲ.ላ.ባውም የተባለ ለፍቶ አዳሪ ሲያስበው በድንገት ተገልጣ ሊያያት ችሏል

9/ በ6.4.1604 ዓ.ም. በጀርመን ሀገር ኢንጉል ስታድት ውስጥ አባ ያዕቆብ ሬም የተባሉ መነኩሴ እመቤታችን ድንግል ማርያም ከምድር ከፍ ብላ በዐየር ላይ ስትንሳፈፍ ሊያዩዋት ችለዋል፤

10/ በ15.12.1631 ዓ.ም. ንግሥተ ሰማይ የተባለች እመቤታችን ድንግል ማርያም በኢጣልያ ሀገር ኔፐልስ በተባለ ተራራማ ቦታ በሚገኝ እርሻ በላይ ሆና ለብዙ ኢየሱሳውያን እየተባሉ ለሚጠሩ ለሃይማኖት ድርጅት ተከታዮች ተገልጣ በዚሁ አካባቢ የሚገኘው ቪሱቪስ የተባለው እሳተ ገሞራ (ቮልካኖ) የሚተፋው ቦታ በቅርብ ጊዜ ውስጥ የሚፈነዳ መሆኑን ነግራ አስጠንቅቃቸዋለች ።

11/ በ1647 ዓ.ም. እመቤታችን ድንግል ማርያም ቢኖሳይረስ አርጀንቲና ውስጥ ለአንዲት ልጃገረድና ለአንድ ጉብል ተገልጣ በዚያ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ንስሃ እንዲገቡ ያስጠነቅቁአቸው ዘንድ አዘዋለች ።

12/ በ8.11.1660 ዓ.ም. ሲሲሲያ ውስጥ ጉልቲዝ በተባለ ቦታ አንድ በደም የተነከረ ሰይፍ በዐየር ላይ ሆኖ የከተማይቱ ነዋሪዎች ሁሉ ወጥተው ለብዙ ጊዜ ሊያዩት ችለዋል ።

13 በ1671 ዓ.ም በፈረንሣይ ሀገር ነዋሪ የሆነች ማርጋሪት ማርዮ አላኩክ የተባለች ወይዘሮ በዓለማዊነት ግብር ፀንታ ትኖር በነበረችበት ዘመን አንድ ጊዜ እመቤታችን ተገልጣለት ነበር ።

ታዲያ ከዚያ በኋላ ዓለም በቃኝ ብላ ገዳም እንደገባች ጌታ በየጊዜው እየተገለጠ ይታያት ነበር ይባላል ።

14 በ1682 ዓ.ም. መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እጆቹና እግሮቹ በምስማር እንደ ደሙ ጐድኑም በጦር እንደተወጋ ሆኖ ከነቁስሉ ቬሮኒካ ጊያላኒ ለተባለች ሮማዊት ወይዘሮ ማርካቶሎ በተባለ ቦታ በገሐድ ታይቷል ።


15/ በ1696 ዓ.ም. ኢኳዶር ውስጥ የኩይቶ ጳጳስ እጅግ በጠና ታመው ዛሬ ይሞቱ ነገ እየተባለ ሀገር ተጨንቆ ይጠበቁ ነበር ። ታዲያ ልዩ ልዩ ድንቅ ተአምራትን በማድረግ የታወቀችው የእመቤታችን ሥዕል ታጅባ ግሎርያ (ሰ ባሔ) የተባለው መዝሙር ሲዘመር ሰማያዊት ንግሥት በገሐድ ተገልጣ ጳጳሱን በተአምር ከሞት አፋፍ መልሳ ቸዋለች ።

ይቀጥላል ፣



# የተሰቀለውን እንሰብካለን

"አይሁድ ምልክትን ይፈልጋሉ የግሪክ ሰዎችም ጥበብን ይሻሉ እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን ይህም ለአይሁድ ማሰናከያ ለአሕዛብም ሞኝነት ነው" ይላል ታላቁ መጽሐፋችን ። ይህ ቃል ለሰነፎች ሞኝነት ሲመስላቸው ለአማኞች ደግሞ ብርታትንና ጥበብን ይሰጣል ። ለምሳሌ በማንኛውም በጐ ሥራ ሁሉ ተባባሪ ያልሆኑ ሥራ ጠሎች ሁሉ ወደ ዘላለም እሳ




...ውን ክርስቶስን ቢሰብኩ በአራቱ የመስቀል መዓዝኖች ይታያሉ ።

www.ethiopianorthodox.org

የሃይማኖት ዓምድ

# የእግዚአብሔር ጠባይዓት (ባሕርያት)

ህላዌያተ እግዚአብሔርን በሚመለከት ሁኔታ ባለፉት ወራት ከ1-4 ተከታታይ የነገረ መለኮት ትንታኔዎች መቅረባቸው ይታወሳል ። አሁን ደግሞ የእግዚአብሔርን ባሕርያት ከሚገልጡት የሃይማኖት ትምህርቶች ጥቂቶቹን ባጭር ትንታኔ እናሳያለን ።

በመሠረቱ "እግዚአብሔር መንፈስ ነው" (ዮሐ 4. 24) ተብሎ እንደተጻፈ እንደ እግዚአብሔርነቱ በሚገባ ዘርዝረን ለማወቅ የሚኖረን ችሎታ የተወሰነ መሆኑን ሳንዘነጋ በተለይ ቸር ከመሆኑ የተነሣ ከፍጥረቱ ጋር በሚያደርገው ግንኙነት በቅዱሳት መጻሕፍት አማካይነት ቅዱስ መንፈስ የሰጠንን ምሥጢራት ብቻ እንጠቁማለን ።

1ኛ እግዚአብሔር በዓለም ምሉእ ስለ መሆኑ ፦

በትንቢተ ኤርምያስ 23.24 "ሰውራሱን የሚሸሽግበት እኔ የማላየው ሥውር ቦታ ሊኖረው ይችላልን? እኔ በሰማይም በምድርም ምሉእ (የሞላሁ) አይደለሁምን ? ይላል ጌታ እግዚአብሔር" የሚል የጽሑፍ ማስረጃ አለ ።

ይህም አባባል ከዚህ በፊት "በፓንቴይዝም" ቲዎሪ እንዳየነው ዓይነት "እግዚአብሔር በሰማይም በምድርም (በመላው ዩኒቨርስ) ምሉዕ ነው" ሲባል

ወደ ገጽ ፲፮ ዞሯል

ት ሂዱ የሚለውን ፍርድ ከመስማት ይልቅ መስቀሉን ተሸክማችሁ የተሰቀለውን ክርስቶስን ስበኩ የሚለውን ቃል መስማትና መምረጥ በተሻላቸው ነበር ።

ምክንያቱም ጌታ ክርስቶስ ለፍርድ በሚመጣበት ቀን ይህ የመስቀል ምልክት ለምስክርነት አብሮ ስለሚመጣ በዚያን ጊዜ በሕይወት ሳሉ መስቀሉን ተሸክመው በኋላው የተከተሉና የተሰቀለውን ክርስቶስን የሰበኩ ፣ የክርስቶስን ጽዋ የጠጡ ፣ መከራ የተቀበሉ ፣ ስለ ክርስቶስ ሕማምና ሞት በየአደባባዩ የመሰከሩ ፣ ስለ ወንጌልና ስለ ሀገር የታገሉ በጠቅላላው የመስቀል አገልጋዮች ሁሉ ከፍጹም እምነት ከመልካም ሥራ ጋር እውነተኛ ፈራጅ ወደ ሆነው ወደ ክርስቶስ ይቀርባሉ ። ወደ ሰማያዊ መንግሥት የሚሄዱበትን መስቀል መሸከም ከማስደሰት በቀር አያስፈራምና ይኸውም ሁላችንም በክርስቶስ ፍርድ ወንበር ፊት ስለምንቆም ነው ።

በዚህ አኳኋን በክርስቶስ መስቀል ደህንነት አለ ፣ መስቀሉን በመሸከም ሕይወት አለ ፣ የተሰቀለውን ክርስቶስን በመስበክ ሙሉ ደስታ አለ ፣ በመስቀል ኃይል የልብ ብርታት የመንፈስ ኃይል አለ ፣ በመስቀል መከራ ብቻ ሳይሆን የሥጋም የነፍስም ደስታ አለ መስቀሉን ተሸክሞ ኢየሱስ ክርስቶስን በመከተል ብፅዕና አለ ፍጹም የሆነ ቅድስናም ለማግኘት ይቻላል ያለ መስቀል የሕይወት ጤንነት የዘለዓለም ደህንነት አይገኝምና ።

በክርስቶስ መስቀል አማካኝነት ረድኤትና ጸጋ ያገኘው ጳውሎስም ሲናገር "ዓለም ለእኔ የተሰቀለበት እኔም ለዓለም የተሰቀልኩበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ በክርስቶስ ኢየሱስ አዲስ ፍጥረት መሆን ይጠቅማል" ብሏል ገላትያ ምዕ 6.ቁ.14 ።

ስለዚህ ክርስቲያኖች ቅዱስ ጳውሎስን ምሳሌ በማድረግ ወደ ዘለዓለም ሕይወት እንድንሄድ መስቀሉን ተሸክመን ስለእኛ በዕለተ ዓርብ የተሰቀለውን ክርስቶስን መስበክና ሕይወታችንንም ከእርሱ ጋር መስቀል ያስፈልገናል ። ምክንያቱም እኛ መስቀልን እንሸከም ዘንድ በመስቀልም መሞትን እንወድ ዘንድ ክርስቶስ መስቀልን ተሸክሞ ታሞና ተሰቃይቶ ስለእኛ በመስቀል ላይ ሞቷልና ነው ። አብረንም ከሞትን ከእርሱ ጋር እንኖራለን የመከራውም የመስቀሉም ወዳጆቹ ከሆን የደስታ የክብር ወዳጆቹ እንሆናለን ።

በሌላ አንፃር ደግሞ ስንመለከት ለክርስቶስ የአፍ ወዳጆችና የሥራ ሳይሆን የስም አገልጋዮች ነን የሚሉ አልፈው አልፈው አይታጡም። መስቀሉን ተሸክመው ስለመስቀሉ የሚሰብኩ የልብ ወዳጆች ግን ጥቂቶች ናቸው ። በተጨማሪም የደስታ የህብት የምግብ ወዳጆች ይኖሩት ይሆናል ቃሉን ትምህርቱን የሚሰሙ ጥሪውን ሰምተው የሚከተሉት ትዕዛዝን የሚፈፅሙ ወዳጆቹ ግን እጅግ ያነሱ ናቸው ።

አንዳንዶቹ ደግሞ ቁራሽ እንጀራ እስኪያገኙ ድረስ ኢየሱስን ይከተላሉ ጥቂቶችም ጽዋውን እስኪጠጡ ድረስ ወደ ገበታው ይቀርባሉ ፤ ተአምራቱንም ያደንቃሉ ። እንዲህ ያሉትም ሰዎች መከራ እስኪደርስባቸው ድረስ ኢየሱስን ይወዳሉ እሱንም ያመሰግናሉ ይመርቃሉ የመስቀል መከራ የደረሰባቸው እንደሆነ ግን ወዲያው ከገበታው ይሸሻሉ ፈጥነውም ክርስቶስን ይክዱታል።ደስታ ወዳጆች እንጀራ ፈላጊዎች በመሆናቸው መስቀሉን ለመሸከም ስለማይችሉ ክልቅሶና ከታላቅ ሀዘን ላይ ይወድቃሉ ። እንዲህ ያሉትም ሰዎች ራሳቸውን ወዳድ በመሆናቸው ክርስቶስን ከመስበክ ፣ መስቀሉን ከመሸከም ይልቅ ሁልጊዜ ግላዊ ጥቅማቸውንና ሥጋዊ ፍላጐታቸውን ማሳደድ ደስ ይላቸዋል ። ከመስጠት ይልቅ መቀበልን ከልቅሶ ቤትም የሠርግ ቤትን ይመርጣሉና ።

"ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታልና ስለእኔና ስለወንጌል ነፍሱን የሚያጠፋ ሁሉ ግን ያድናታል ፤ ሰው ዓለም[illegible] ነፍሱንም ቢያጐድል ምን ይጠቅመዋል ? ሰውስ ስለ ነፍሱ ቤዛ ምን ይሰጣል ? ይላል ታላቁ መጽሐፍ ሰው ዓለምን ሁሉ ቢገዛ ሀብቱንም ሁሉ ቢሰጥ የሕይወቱ ዋጋ ሊሆን ስለማይችልና ኢምንት ነው ብዙ መልካም ሥራ ቢሠራ የክርስቶስ መስቀል ካልተጨመረበት በቀር በጣም ጥቂት ነው እውቀትን ሁሉ ሰብስቦ ቢይዝ ነፍሱን ከአጐደለ ገና አላዋቂ ነው ታላቅ ኃይል ቢኖረውና መልካም ስምም ቢሰጠው በክርስቶስ መስቀል ካልተመካና መስቀሉንም የመንገድ ጥርጊያ ተከትሎ ካልተጓዘ ታላቅ ኃይልም ቢኖረው የመንፈስ ደካማ ነው ።

ይህም ማለት አንድ ክርስቲያን ከክርስቶስ በቀር ሁሉን ነገር ቢተው ሌላው ቀርቶ ራሱን እንኳን ሳይቀር ቢጠላ ለሃሳቡም ለፈቃዱም ተገዥ እንዳይሆንና የዓለምም ፍቅር እንዳይዘው ሊሠራው የሚገባውን ቢሠራ ይህን ሠራሁ ይህን አደረግሁ ብሎ እንዳይመካ ይሁን ማለት ነው ።

ይህም እንዲሆን በመንፈስ መሞላት ያስፈልጋል ፖስካል የተባለው ሊቅ "በሰው ሕይወት ውስጥ ባዶ ቦታ አለ ። ይህንንም ባዶ ሥፍራ ማንኛውም ነገር ቢጠራቀም ሊሞላው አይችልም ። ነገር ግን በእግዚአብሔር መንፈስ ሊሞላ ይችላል" ብሏል ።

እንዳለውም በክርስቶስ መንፈስ ካልተሞላን ክርስቶስ ባዶ መሆናችንን ስለሚያውቅልን መከራውን ወደ ደስታ መስቀሉንም ወደ ክብር ይለውጥልናል ሥራችንንም ይባርክልናል ምክንያቱም በክርስቶስ መስቀል የመንፈስ ባለፀጋ ፣ በክርስቶስ ሕማም ኃይለኛ ፣ በክርስቶስ ሞት ነፃ መሆን ስለምንችል ነው ።

እንግዲህ አዲስ ፍጥረት እንድንሆንና መንፈሳዊውም ሆነ ሥጋዊው ጥበብ እንዲገልጥልን በምንሠራው ሥራ ሁሉ ስለ እኛ የተሰቀለውን ክርስቶስን እንስበክ ።

www.ethiopianorthodox.org

## የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ዜና

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክርስቲያን 100 ሽህ ብር ሰጠች ።

ጥር 30 ቀን 1971 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በተፈጥሮ አደጋና በሰው ሠራሽ ችግር ለተጎዱት ወገኖቻችን በመንግሥት ለታቀደው ዘላቂ መፍትሔ መርጃ ይሆን ዘንድ አንድ መቶ ሽህ ብር መስጠትዋ ተገለጠ ። የአንድ መቶውን ሽህ ብር ቼክ የሰጡ የኢትዮጵያ ኦ.ተ.ቤ/ክርስቲያን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ናቸው ።

የኦ. ተዋሕዶ ቤ/ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ በሰጠው ውሳኔ መሠረት ከቤተ ክርስቲያን ሣጥን የተለገሰውን ገንዘብ ከቅዱስነታቸው የተቀበሉት የርዳታ ሰብሳቢ ቡድን ኃላፊ ሻለቃ ተካልኝ ባልቻ መሆናቸው ተገልጦአል ። በሥነ ሥርዓቱም ላይ የቅዱስ ሲኖዶስ ዓባላት የሆኑ ጳጳሳት እንዲሁም የርዳታ ሰብሳቢ አጠቃላይ አስተባባሪ ኮሚቴ ሹማምንትና ዓባላት ተገኝተዋል ።

ኩባ ፦ ቅዱሳት መጻሕፍት በብዛት ወደ ኩባ እንዲገቡ ተጠየቀ

በ1977 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ.) በኅዳር ወር የተባበረው የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ወደ ኩባ ቅዱሳት መጻሕፍትን በግልጥ አስገብቷል ። ሕዝቡም መጽሐፍ ቅዱስን ለማግኘት የጋለ ፍላጎት ነበረው ። በጥር ወር 1979 (እ.ኤ.አ.) ደግሞ እንደገና አንድ ኢክዩሚኒካል (ዓለም አቀፍ) የሆነ ድርጅት የኩባ ባለ ሥልጣኖችን በማስፈቀድ ለኩባ አብያተ ክርስቲያናት ቅዱሳት መጻሕፍትን ያከፋፍላል ። የኩባ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ በቅርቡ ተጠይቀው እንደገለጡት በኩባ የሕዝብ ቋንቋ በእስፓኒሽ አዲስ ኪዳን ታትሞአል እንደዚሁም በኩባ የሚገኙ የመንፈሳዊ ትምህርት (የቴዎሎጂ) ሰሚናሪዮዎች በግሪክ ፣ በዕብራይስጥና በሌሎችም ቋንቋዎች የታተሙ ቅዱሳት መጻሕፍት እንዲገቡላቸው የተባበረው የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበርን የጠየቁ መሆናቸው ተገልጦአል ።

ወርልድ ሪፖርት ቁጥር 107/4
የካቲት 1979 (1971)

የቤተ ክርስቲያን መስፋፋት በምሥራቅ ጀርመን

በርሊን ጀርመን ፦ በኅብረተሰብአዊት ምሥራቅ ጀርመን በአዳዲስ ከተማዎች ሁሉ አብያተ ክርስቲያናትን ለመሥራት የገንዘብ አስተዋጽኦ በመደረግ ላይ ነው ። "በአዳዲስ ከተማዎች አዲስ ሰበካዎች እንዲቋቋሙ የጀርመን መንግሥት መስማማቱ በሶሻሊስት ሀገሮች ላሉ ክርስቲያኖች ሊስተዋል የሚገባ አስፈላጊ ነገር ነው" ሲሉ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ፌዴሬሽን ጽ/ቤት ዳይሬክተር አቶ ማንፈረድ ስቶፕል ጠቁመዋል ። አቶ ስቶፕል በምሥራቅ ጀርመን ራዲዮ ባደረጉት ንግግር ቀሳውስትን የሰበካ ጉባኤ መሪዎችንና የቤ/ክርስቲያን አባላትን በኅብረተሰብአዊት ጀርመን የክርስትና እምነት እንዲስፋፉ ስላደረጉት ጥረት አመስግነዋል ። ከዚህ በፊት በ1978/1970/ ዓ.ም. አብያተ ክርስቲያናት ለመሥራት የወጣው ልዩ ፕሮግራም በጀርመን መንግሥት ተደግፎአል ። በዚህ ፕሮግራም መሠረት የሚሠሩት የሐዲሳን አብያተ ክርስቲያናት ቁጥር 50 እንደሚሆን በየካቲት ወር 1979 (1971) ዓ.ም የወጣው ኢክዩሚኒካል ፕሬስ ሰርቪስ በቁ. 4/46ኛ ዓመት እትሙ ገለጠ ።

በ1973 (1981) ዓ.ም. አዲስ ቤተ ክርስቲያን በምሥራቅ ጀርመን ትመሠረታለች ።

በርሊን ጀርመን ፦ በዲሞክራሲያዊትና ሕዝባዊት ጀርመን ውስጥ በ1973 (1981) ዓ.ም አዲስ ቤ. ክርስቲያን ትቋቋማለች ። ቤ. ክርስቲያንዋ የተባበረችው የፕሮቴስታንት ቤ. ክርስቲያን ተብላ ትጠራለች ። በምሥራቅ ጀርመን የሚገኙ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ፌዴሬሽን ፤ የሉተራን ወንጌላዊት ቤ. ክርስቲያንና የኅብረት ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን በአንድነት ተዋሕደው ከላይ በተጠቀሰው ስም ይሰየማሉ ። የዚች የአዲስ ቤተ ክርስቲያን ሕግ በ1973 (1981) ዓ.ም ይወጣና እንዲሠራበት ይሆናል ። ሕጉ ሥራዎችን ይወስናል ጠቅላላ ሲኖዶስንና አስተዳደርንም የሚመለከት ደንብ ያወጣል ።

ኢክዩሚኒካል ፕሬስ ሰርቪስ ቁ. 4/46ኛ ዓ
የካቲት 1979 (1971)

የግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበርን በግልጥ ጎበኙ

ጀኔቫ ፦ የግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ሲኖዳ ሣልሳዊ ባለፈው የካቲት ወር 1971 ዓ.ም. ለሦስት ቀናት የዓ.አ.ክ. ማኅበርን ለመጀመሪያ ጊዜ በጀኔቫ ጎብኝተዋል ። ፓትርያርኩ ከዓ.አ.ክ.ማ. ዋና ጸሐፊ ከዶ/ር ፊልጶስ ፓቴርና ከሌሎችም ባለሥልጣኖች ጋር ተገናኝተው ቤተ ክርስቲያንን ስለሚመለከት ጉዳይ ተወያይተዋል ። ሣልሳዊ ሲኖዳ በአሁኑ ጊዜ የ56 ዕድሜ ሰው ሲሆኑ የወንጌላዊው የማርቆስ 117ኛ በዓለ መንበር ናቸው ። ቅዱስነታቸው የስድስት ሚልዮን ጠንካራ ክርስቲያኖች መንፈሳዊ አባት ናቸው ። ፓትርያርክ ሲኖዳ እግረ መንገዳቸውን ታላቅዋ ብሪታንያን ጎብኝተዋል ።

ኢክዩሚኒካል ፕሬስ ሰርቪስ ቁ4/46ኛ ዓ.
የካቲት 1979 (1971)

የባንግላዴሽ ክርስቲያኖች አፈሻል ድጋፍን አገኙ

ዳካ ባንግላዴሽ ፦ ያለፈው የልደት በዓል የባንግላዴሽ ርእሰ ብሔር በተገኙበት በባንግላዴሽ ዋና ከተማ በዳካ ተከብሮ ውሎአል ። የባንግላዴሽ ርእሰ ብሔር ሜጀር ጄኔራል ዚአውር ራህማን በበዓሉ ላይ ለተሰበሰበው ሕዝበ ክርስቲያን ባደረጉት ንግግር "ሁሉም የባንግላዴሽ ዜጋ በመሆኑ እየኮራ ሀገሩን በሚመለከት ጉዳይ ሁሉ ተሳትፎ ማድረግ አለበት" ብለዋል ። በባንግላዴሽ የሚገኘው ማኅበረ ክርስቲያን ፦ በእርሻ ፣ በጤና በቤተሰብ ፕላንና በትምህርት የረጂም ጊዜ ልማት እንደጀመረ ርእሰ ብሔር ዚአውር አስረድተዋል ሲል ኢክዩሚኒካል ፕሬስ ሰርቪስ በጥር ወር (1979/1971) ባወጣው እትሙ ቁ. 3/46ኛ ዓመት ገለጠ ።

# ቤተ ክርስቲያንና ቅርሶችዋ

ጉንዳ ጉንዲ ማርያም

ጉንዳ ጉንዲ ማርያም በትግራይ ክፍለ ሀገር በአጋሜ አውራጃ በሣዕሣዕ ስቡሕ ወረዳ ከአዲ ግራት ከተማ በስተምሥራቅ በኩል አምሣ ኪሎ ሜትር ያህል ርቆ ይገኛል ። የጉንዳ ጉንዲ የመሬት አቀማመጥ በጣም ዝቅተኛ ቆላማ ስፍራ ከመሆኑም ሌላ በኢትዮጵያ ከሚገኙት በጣም ዝቅተኛ ስፍራዎች አንዱ ሲሆን የጂኦግራፊ ሊቃውንት ይህ አካባቢ ከባሕር ወለል በታች 100 ሜትር ያህል ዝቅ ብሎ ይገኛል ተብሎ ከተመሰከረለት ደሉል የተባለው የመዓድን ስፍራ የስድስት ሰዓት የእግር መንገድ ርቆ የሚገኝ በመሆኑ የአየሩ ጠባይ ክረምትም ሆነ በጋ በጣም ሞቃት ነው ።

ጉንዳ ጉንዲ በጣም ዝቅተኛ ስፍራ ለመሆኑ ዋናው ማስረጃው ከአዲ ግራት ተነስቶ ወደዚህ ገዳም ለመሄድ በሚደረገው የእግር ጉዞ የአንድ ሰዓት የእግር መንገድ ሜዳማውን ሥፍራ ከቋረጡ በኋላ የሚደረገው ጉዞ ከረጅም ፎቅ ተነሥቶ ወደ ምድር ቤት እንደሚወርድ ሰው ቀኑን ሙሉ ቁልቁል ሲወርድ መዋል ነው ። መንገዱ ቁልቁለት መሆኑ ብቻ ሳይሆን በሹል ድንጋይ የተገነቡት የአካባቢው ተራሮችና ኮረብታዎች እንግዳ ሰው መግቢያውንና መውጫውን ሊያውቀው አይችልም ።

ጉንዳ ጉንዲ ምንም እንኳን ቆላማና ፀሐያማ እንደዚሁም ድንጋይና አለት የበዛበት ስፍራ ቢሆንም በገዳሙ አጠገብ አልፎ የሚፈስ ዋዕራት የተባለ ወንዝና ጥቂት የውሃ ምንጮች ስለአሉ በሸለቆው ውስጥ ጥቂት ልምላሜ ያል ተለያቸው የቆላ ዕፀዋት ሲገኙ የገዳሙ መነኰሳት ያለሙት የሙዝና የብርቱካን የፓፓያ የትርንጎ እረንጓዴ ተክሎች ይገኙበታል ። በአካባቢው በሚገኙት ተራሮችዋ አልፎ አልፎ ትንንሽ ቁጥቋጦች ይታዩባቸዋል ።

በጉንዳ ጉንዲ አካባቢና ከዚያም አልፎ የጨው ፤ የድኝ ፤ የብረት ፤ የፓተሽ ፤ የተፈጥሮ ጋዝ ወዘተ የመሳሰሉት የተፈጥሮ ማዕድናት ክምችት የሚገኙበት የደሉል በረሃ አካባቢ በሙሉ ስፍራው ከብት ግመል ፍየልና በግ እያረቡ የሚኖሩ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች የሆኑ የሳሆ ብሔረ ሰቦች ናቸው ይህም በመሆኑ የጉንዳ ጉንዲ መነኰሳት በትግርኛና በሳሆኛ ቋንቋ ይናገራሉ ።

ታድያ የጉንዳ ጉንዲ ገዳም የመሬቱ አቀማመጥ ለመኖር በጣም አስቸጋሪ ሲሆን እንዴት ሊመሰረት ቻለ እስከ አሁን ድረስስ እንዴት ያለ አንዳች ጥፋትና ድምሳሴ ሊኖር ቻለ?

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተርክስቲያን ታሪክ በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አንሥቶ እስከ 15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ከፍ ያለ የሃይማኖት ብጥብጥ ተነሥቶ ነበር።

ይህም የሃይማኖት ብጥብጥ ሊነሣ የቻለው በሽሬ አውራጃ ቆየፃ ከተባለው ገዳም አባ ሳሙኤል ዘቆየፃ ከተባሉ ጻድቅ ከልጅነቱ ጀምሮ ሲማር ያደገ አባ እስጢፋኖስ የተባለ መነኩሴ በመጻሕፍተ ብሉያትና ሐዲሳት እጅግ የተራቀቀ ሊቅ መነኩሴ ስለነበር በሚያደርገው የሥነ መለኮት መራቀቅ በአካባቢው ከነበሩ መነኰሳት ጋር ሳይግባባ በመቅረቱ ተቀዋሚዎቹ መነኰሳት ለመስቀል አይሰግድም ፀረ ማርያም ነው እያሉ በአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ከሰሱት ከዚህም የተነሣ ብዙ ግፍና ሥቃይ ደርሶበት በዚያውም ላይ ተሰዶ በሄደበት ገዳምና ስፍራ ሁሉ መጠጊያና ማረፊያ በማጣቱ እርሱና ተከታዮቹ ገዳማት በብዛት ከማይገኙበትና በአካባቢው ክርስቲያኖች ከማይበዙበት አካባቢ በመፈለግ ለዚሁም አላማው የጉንዳ ጉንዲ የመሬት አቀማመጥ በጣም ጥሩ ሆኖ አገኘው በጊዜው ከነበሩት ባላባቶች ጋራ ተነጋግሮ እርሱና ተማሪዎቹ የጉንዳ ጉንዲን ገዳም ሊመሠርቱ ችለዋል ።

አባ እስጢፋኖስ ይህንን ገዳም እንደ መሠረተ የርሱን ትምህርት የሚከተሉና በፍልስፍናው የሚመሩ በሌላ ገዳም ይኖሩ የነበሩ መነኰሳት ሁሉ ከየገዳማቱ እየተባረሩ ወደ ጉንዳ ጉንዲ ተሰደዱ ።

በዚያን ዘመን አባ እስጢፋኖስን ይከተሉ የነበሩ ሁሉ ደቂቀ እስጢፋኖስ የሚል መጠርያ ስም ሲኖራቸው እንደ መምህራቸው በትምህርታቸው የበሰሉ ፍጹማን መናንያን ለቆሙላት ዓላማ ሞትንና ስደትን የማይፈሩ ከነገሥታትና ከመኳንንት ፊት ቀርበው ተከራካሪዎቻቸውን ከብሉይና ከሐዲስ እየጠቀሱ ተገቢውን መልስ የሚሰጡ ሊቃውንቶች ነበሩ ።

ከዚህም የተነሣ በመላው ኢትዮጵያ ስማቸው በመናፍቅነት ይጠራ ስለ ነበር መአርገ ክህነት እንዳያገኙ ተከልክለው ነበር ክህነት ከመከልከላቸው የተነሣ የያዙትን ሃይማኖት ትክክለኛ ለመሆኑ ነገር ግን በምቀኝነት ብቻ ለብዙ ዘመናት ብዙ ግፍ እንደደረሰባቸው ለማስረዳትና ከተቃዋሚዎቻቸው ጋር በትክክለኛ መንገድ ተከራክረው ለመርታት ወይም ለመረታት በማሰብ ከሌሎች ከተቃዋሚዎቻቸውና ከደቂቀ እስጢፋኖስም ዕዝራ በተባለው ሰው መሪነት ከኢትዮጵያ ወደ እስክንድርያ ፓትርያርክ ሄደው ከዚህ በሚከተለው መንገድ ተከራክረው እንደ አሸነፉ ገድለ እዝራ እንደዚህ ይላል ።

ከዚህም በኋላ የኢትዮጵያ መነኰሳት በግብጽ ጳጳስ ዘንድ ከሰሱአቸው ። የክሱም አሳብ እንዲህ የሚል ነበር ። "እነሆ መነኰሳት ያይደሉ መነኰሳት መጥተዋል ... በሥላሴ አያምኑም ፤ ለማርያምና ለመስቀል አይሰግዱም ታቦት የላቸውም ቁርባን አይቆርቡም ሲጸልዩም አቡነ ዘበሰማያትና ጸሎተ ሃይማኖትን አይደግሙም ። በጳጳስ ተወግዘዋል ሕጋቸውም እንደ ሕጋችን አይደለም ። የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ አባ ዮሐንስም ይህን ከሰማ በኋላ ጉባኤ አደረገ የቤተ ክርስቲያንን ሕግ የሚያውቁ የግብጽ ሊቃውንትንም ጠራ እነዚያ ከሳሾች መነኮሳት ለብቻቸው ቆሙ ፤ አባ እዝራም ከወንድሞቹ ጋር ለብቻው ቆመ ።ከዚህ በኋላ አባ እዝራ "ፈራጅ የሰጠን እግዚአብሔር ይመስገን" በማለት ነገሩን ማስረዳት ጀመረ ። "ሃይማኖታችንን እንድናሰማ ወደዚህ የመጣን እኛ ከሐዋርያው ከማርቆስ መንበር የተገኘን ያዕቆባውያን ነን እንጂ እነዚህ እንደሚሉት ሌላ ሃይማኖት የለንም ።

አብ በአየርና በባሕሮች ጥልቀት የሚያበራ ፀሐይ ነው ። ወልድ በሰማያትና በባሕሮች ጥልቀት የሚያበራ ፀሐይ ነው ። መንፈስ ቅዱስም በሰማያትና በባሕሮች ጥልቀት የሚያበራ ፀሐይ ነው ። እግዚአብሔር ሥሉስ ገጽ ዋሕደ መለኮት ነው ሃይማኖታችን ይህ ነው ለማርያምም እንሰግዳለን ለእሳተ መለኮት ማኅደር ሆናለችና የዚህ ዓለም ኃጢአትም አልነካትምና ። ለመስቀልም እንሰግዳለን የመከራው አልጋ ነውና ነቢይ ስለእርሱ እንዲህ ይላል በስተምሥራቅ የተተከለ ዛፍ አየሁ ከፍሬውም ለተመረጡት ይሰጣል ይህም ስለ መስቀል ነው ። ሰሎሞንም እንዲህ ይላል ከጥላው በታች ለማረፍ ወደድሁ ፍሬውም ለጉሮሮዬ ጣፋጭ ነው ። የመስቀል ፍሬ ማለት የክርስቶስ ሥጋና ደም ነው የተመረጡ የተባሉም ስለ ስሙ የሞቱ ሰማዕታት ናቸው ። ታቦት የላቸውም ስለሚሉት ጉዳይ እንደዚህ ነው እርግጥ ኦሪት "ቁመቱ ሁለት ክንድ ተኩል ፣ ወርዱ አንድ ክንድ ተኩል የሆነ ታቦት ከማይነቅዝ እንጨት ሥራ" ትላለች ። ታቦት ማለት የሁላችንና የመላእክት መመኪያ የሆነች ማርያም ናት ።አቡነ ዘበሰማያትን አይጸልዩም ስላሉትም ጌታ በወንጌል ለደቀመዛሙርቱ "ስትጸልዩ አቡነ ዘበሰማያት በሉ ሲል አስተምሮአቸዋልና እኛም እንጸልያለን ። ስለ ቅዱስ ቁርባን መቀበልም " ... በእምነት ሥጋውንና ደሙን የሚቀበል የዘለዓለም ሕይወት ይኖረዋል" ይላልና ይህን ትእዛዝ እየሰማን የማንቀበል ከሆንን እንደ ዕውራን ነን ነገር ግን በቅንዓታቸው ይከሱናል" ገድለ እዝራ ገጽ 76 1954 ዓ.ም. የታተመ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ግን ስለታቦት ጉዳይ የእነ እስጢፋኖስን ትምህርት አትቀበልም ።

አባ እዝራ በዚህ ዓይነት መሠረታዊ ጥቅስ የአባቱ የእስጢፋኖስን ሃይማኖት ለግብፅ ጳጳስና ሊቃውንቶች በማስረዳት ተቀዋሚዎችን ካሳፈረ በኋላ በኢትዮጵያ የተነፈገውን መዓርገ ዲቁና ለርሱና ለተከታዮቹ እንዲሰጥ ተፈቀደ እዝራና ተከታዮቹ በእስክንድርያ ለጥቂት ዓመታት ከተቀመጡ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ከሶርያው ሊቀ ጳጳስ መዓርገ ቅስና ተቀብሎ ወደ አገሩ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሶአል ከርሱ ጋራ የሄዱት መነኮሳት ግን ከመንገድ ሞተው ቀርተዋል ።

ሊቁ እዝራ ወደ አገሩ እንደተመለሰ እንደአባቱ እንደ እስጢፋኖስ ወደ ነገሥታት ቤት እየተጠራ ከኢትዮጵያ ሊቃውንቶች ዘንድ በሃይማኖት ክርክር በማድረግ ብዙ ጊዜ አሸናፊ በመሆን ወጥቶአል ከዚያ ወድያ ግን የደቂቀ እስጢፋኖስ ሃይማኖት ትክክለኛ መሆኑ እየታወቀ በመሄድ በመላዋ ኢትዮጵያ ትምህርታቸውንና ጥበባቸውን በግልጽ ለማስፋፋት ችለዋል ።

የደቂቀ እስጢፋኖስ ሞያ በቀላል ተከራክሮ ብሉይና ሐዲስ ጠቅሶ ተቀዋሚዎቹን ማሳፈር ብቻ ሳይሆን በእደ ጥበብ በኩል በጣም ተደናቂ የሆነ እውቀት ነበራቸው ። ይኸውም መጻሕፍት መጻፍ ፡ ስዕል መሳል ፡ መስቀል መቅረፅ ሐረግና ቅርፃ ቅርፅ መሥራት የመሳሰሉት ሞያዎች ከፍተኛ የሆነ ችሎታ እንደነበራቸው በአሁኑ ጊዜ ካሉት ጥንታውያን ገዳማት አልፎው አልፎው ይገኛሉ ።

ከሁሉም ይበልጥ ደግሞ የግራኝ መሀመድ የእሳት ወላፈን ሳያገኛቸው ተደብቀው የቀሩ የደቂቀእስጢፋኖስ የሥራ ውጤቶች የሆኑ ቅዱሳት መጻሕፍትና ዕፀ መስቀላት እስከ ስዕላቸውና ሐረጋቸው በጉንዳ ጉንዲ ገዳም ተከማችተው የሚገኙ ስለሆነ በዚያን ጊዜ የነበሩ መነኰሳት ምን ያህል ቀለማዊና ተግባራዊ የሆነ ረቂቅ ጥበብ እንደነበራቸው ለመገመት አያዳግትም ።

የጉንዳ ጉንዲ የአመሠራረት ታሪክ እንደዚህ ይሁን እንጂ በ1968 ዓ.ም. ታሪካዊ ጥናት ለማድረግ ወደዚህ ስፍራ ሄጄ በነበረበት ጊዜ የገዳሙ ሁኔታ ከዚህ በሚከተለው ሁኔታ ነበር ።

በአሁኑ ጊዜ በጉንዳ ጉንዲ ማርያም ገዳም ጠቅላላ ነዋሪዎች 51 ሲሆኑ ከነዚህ መካከል ሠላሳ ሰዎች መዕርገ ክህነት ያላቸው መነኰሳት ሲሆኑ ሃያ አንዱ ደግሞ ተማሪዎችና አርድእቶች ናቸው የዚህ ገዳም አበምኔት መምህር ወልደ ዮሐንስ ወልደ ሥላሴ የሚባሉ ሲሆኑ መጋቢው ደግሞ አባ ገ መድህን ወ ሩፋኤል ይባላሉ ከመነኮሳቱ መካከል አንዱ የመጽሐፍ አንዱ የመዝገብ ቅዳሴ አንዱ የንባብ መምህራን ይገኙባቸዋል ።

የዚህ ገዳም ነዋሪዎች ይተዳደሩ የነበረው ቀደም ብሎ በነበረው የጉልታዊ ሥርዓት መሠረት በዓመት ከ350 ኲንታል በላይ ገቢ የሚያስገኝ ጉልተ ርስት ነበራቸው በተጨማሪ መነኮሳቱ ራሳቸው ያለሙት የሙዝ ፤ የብርቱካንና የፓፓያ ተክል በሚገባ እየተከሉና እያስፋፉ እስከ አዲግራት ድረስ በአህያ ጭነው በመውሰድ እየሸጡ ይጠቀሙ ነበር።በአሁኑጊዜም ይህንኑ የአትክልት ሥፍራ በከፍተኛ ደረጃ በማስፋፋትና በዘመናዊ ዘዴ አትክልቱን በመትከል ለዕለት ጉርሳቸውና ለአመት ልብሳቸው ያገኛሉ በተጨማሪም በጉንዳ ጉንዲ አካባቢ የዘንባባ ዛፍ በብዛት ስለሚበቅል ለምንጣፍና ለሞተ ሰው መገነዣ የሚሆን ሰሌንና የልዩ ልዩ እቃ መያዣ የሚሆን ዘንቢልና የሰሌን ቆብ በመሥራት እንዲሁም ጥሕሎ የተባለውን የአጋሜ ሕዝብ ምግብ መብልያ የሚሆን ሸንጣራ መውግያ የተባለ እንጨት እያዘጋጁ በአዲግራት ከተማ በመሸጥ ራሳቸውን ችለው ይኖራሉ ። ገዳሙ





www.ethiopianorthodox.org

የሚተዳደረው በአንድነት በመሆኑ ከየአቅጣጫው የሚገኘውን ገቢ በአንድነት ሆነው ይመገባሉ ይጠጣሉ ይለብሳሉ ።

ከላይ ከፍብየ እንደገለጽኩት ሁሉ ደቂቀ እስጢፋኖስ መጻሕፍት በመጻፍ ሥዕልና ሐረግ በመሳል መስቀል በመቅረፅ በመሳሰሉት እደ ጥበባት በጣም የታወቁ እንደነበሩ ገልጬ ነበር በዚህ ረገድ በጉንዳ ጉንዲ ገዳም ውስጥ በዓይነታቸውና በጥራታቸው በስዕላቸውና በሐረጋቸው በአቀራረፃቸው እጅግ አስደናቂ የሆኑ ቅዱሳት መፃሕፍትና መስቀሎች አክሊሎች ሌሎች ቅርሳ ቅርሶችም በሚከተለው መንገድ ተከማችተው ይገኛሉ ።

1ኛ ከ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ የተጻፉ ከ250 በላይ ቅዱሳት መጻሕፍት

2ኛ ስድስት የወርቅ ቅብ ዘውድ

3ኛ ሦስት የብር አክሊል

4ኛ ሁለት የወርቅ መስቀል

5ኛ አራት የብር መስቀል

6ኛ ስድስት የነሐስ መስቀል

7ኛ ሁለት የመዳብ መስቀል

8ኛ ዕፀ መስቀል

9ኛ ሁለት ድባብ

10ኛ አንድ መሰቦ ወርቅ

11ኛ ሁለት የወርቅ ጽዋዕ

12ኛ ሁለት የብር ፃህል

13ኛ አራት ጥንታዊ ጽንሐ

ከዚህ ላይ ከተጠቀሱት ጥንታውያን መጻሕፍት መካከል አስደናቂ የስዕል ጥበብ የተመላባቸው መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው ።

1ኛ ሦስት አርባዕቱ ወንጌላት በየታሪካቸው የተሳሉ

2ኛ 3 ተአምረ ማርያም በየታሪካቸው የተሳሉ

3ኛ መጽሐፈ ሄኖክ በየምዕራፉ የተሳለ

4ኛ ደቂቀ ነቢያት በየምዕራፉና በየታሪኩ የተሳለ

5ኛ ገድለ መዝገበ ሥላሴ በየታሪኩ የተሳለ

6ኛ ገድለ ተክለ ሃይማኖት በየታሪኩ የተሳለ

እነዚህ ከላይ የጠቀስናቸው መጻሕፍት በጠቅላላ ስላቸውና ሐረጋቸውን የተመለከተ ሰው በዚያን ጊዜ የነበሩ ሠዓሊዎች ምን ዓይነት ችሎታ እንደነበራቸው ለመገመት ያስችለዋል ።

ከሁሉም ነገር የሚያስደንቀው ነገር ቢኖር የጉንዳ ጉንዲ ገዳም የተመሰረተው ከግራኝ መሐመድ ወረራ በፊት ነበር ይሁን እንጂ በዚያን ጊዜ ዝነኛ የነበሩ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት አድባራት እስከነ ንዋየ ቅድሳታቸው ተቃጥለው ሲያልቁ የጉንዳ ጉንዲ ገዳም ግን አንዲት ቁራጭ ብራና አልጠፋችበትም ለነገሩ ግን የጉንዳ ጉንዲ አመሠራረት ከግራኝ መሐመድ ሃይማኖት ተከታዮች ያልራቀና ያልተሰወረ ነበር እንደምገምተው ከሆነ ግን ይህን ገዳም ሳያቃጥል የቀረው የጉንዳ ጉንዲ መነኮሳት በቤተ መንግሥትም ሆነ በቤተ ክህነት እንደ አረማውያን እንጂ እንደ ክርስቲያኖች የማይቆጠሩና በየጊዜው ሞት ፣ ስደት ፣ ግርፋት ይደርስባቸው ስለነበር በግራኝ ጊዜ ወራሪ የነበሩ እንደ ቤተሰብ ቆጥረዋቸው ሊሆን ይችላል ።

ግርማ ኤልያስ

## የእግዚአብሔር ጠባይዓት

ከገጽ ፲፱ የዞረ

እግዚአብሔር ራሱ ይህን ዓለም ተዋሐደ ወይም ከዚህ ዓለም ጋር የተደባለቀ ወይም ሥረ ወጥ ሥሪት አድርገን መመልከት ስሕተት መሆኑን በቅድሚያ መገንዘብ ይገባል ። የሃይማኖት ዋና መሠረቱ እግዚአብሔር ከዓለም (ከዩንቬርስ) የተለየና ከርሱም በፊት የነበረና ያለ ኋላም ይህን ዓለም ካለመኖር ወደ መኖር ያሸጋገረ እርሱ መሆኑን ማመንና መቀበል ነው ። እግዚአብሔር በዓለም ሁሉ ምሉእ ነው በምንልበት ጊዜ ፣ ሁሉ በርሱ የሆነ ያለርሱ ምንም ያልሆነ ። ሁሉን ነገር መርምሮ የሚያውቅ እርሱ ለፍጥረት ሁሉ ሥውር ቢመስልም ፍጥረት ለርሱ ግልጥ መሆኑን ለማሳየት ያህል ነው ። ስለዚህም አባባል የቃል ሐተታ እምብዛም ሳያስፈልገን በጽሑፍ የተደገፈ ማስረጃ አለ ። ይህንም ከሞላ ጎደል ለመገንዘብ የ"የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት" በሚል ርእስ በተጻፈውና በሌሎችም መጻሕፍት መመልከት ይቻላል ።

ዳዊት በመዝሙሩ "ምድር (ዓለም) በመላዋ የእግዚአብሔር ናት" ሲል ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ "ዓለምና በዓለም ያለው ፍጥረት ሁሉ ሕይወት አግኝቶ የሚኖር በርሱ ነው" ይላል ። (መዝ.24 1 ፣ የሐዋ 17.28) በሌላም ክፍል "ወደ ሰማይ ብወጣ አንተ እዚያ አለህ ፣ ወደ ምድር ጥልቀትም (ቀላይ) ብወርድ አንተ እዚያም አለህ ፣ በክንፍም ፣ እስከጽንፈ ምድር ብበር አንተ የሌለህበት ሥፍራ የለምና ክንድህ በዚያ ትመራኛለች" ይላል (መዝ 139.8)

እንግዲህ እግዚአብሔር በዓለም ምሉእ ነው ሲባልም ዓለምን እርሱ እንደሚወስን እንጂ ዓለም እርሱን እንደምትወስነው አድርጎ ለማቅረብ መሞከር ስህተት ነው ። እርሱ በሰማይም በምድርም መኖሩን የመግለጥ ሁኔታዎች ሁሉ የሚጠቁሙን ዋና ነገር የሁሉ መሠረት እርሱ መሆኑንና ከሆነው ነገር ሁሉ ያለርሱ ምንም ምን አለመኖሩን ብቻ ነው ።

2ኛ እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ (ከሃሊ) ስለመሆኑ

የእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነት የሚገለጥባቸው ብዙ ጠባይዓት አሉ ፦ ለምሳሌ ያህል ፣ ኃያልነቱ ፣ ፈጣሬ ዓለማት መሆኑ ፣ ለዓለም መልክ ልክና ወሰን ለይቶ ሚዛናዊ አቋም መስጠቱ የፈጠረውን ፍጥረት ሁሉ ሰፍሮ ቆጥሮ በማወቅ መጠበቁ መመገቡና ማስተዳደሩ ጠዘተ በቅዱሳት መጻሕፍት ተገልጠዋል ። እርሱን የሚወስነውም ፈቃዱ ብቻ እንጂ ሌላ ወሳኝ ኃይል የለበትም ። ስለዚህም ዳዊት በመዝሙሩ ሲያስረዳ እግዚአብሔር በሰማይም በምድርም በቀላያትና በባሕርም ሁሉ የፈቀደውንና የፈለገውን ሁሉ አደረገ (ያደርጋል) አለ (መዝ 115.3) ይህም አባባል ከፈቀደ ሁሉን እንደሚሠራ ካልፈቀደ ግን ቢተወው አዛዥ ናዛዥ እንደሌለበት ያስገነዝባል ማለት ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ ሁሉን ነገር ሲሠራ ዓላማ አለው አብዛኛውን ለሰው ጥቅም እንዲውል አድርጎ መፍጠሩ እሙን ነው ። በመጽሐፈ ኢዮብ ስለእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነት ሲገልጥ "ሁሉን ታደርግ ዘንድ ቻይ እንደሆንህ እኔ አውቃለሁ ሃሳብህንም ይከላከል ዘንድ የሚችል የለም" የሚል ተጽፎ ይገኛል ኢዮ 24.2 መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልም (በሉቃ 1.37) ለእግዚአብሔር የሚሣነው ምንም ነገር የለም ማለቱ ይታወሳል ።

ስለዚህ የርሱን ከሃሊነት (ሁሉን) ቻይነት ለመገንዘብ ከዚህ በላይ በሰዎችም በመላእክትም አድሮ ቅዱስ መንፈስ ያናገራቸው ቃላት በቂ ናቸው ። ስለዚህም እግዚአብሔር በተግባሩ ሁሉ ይህ ቀረህ የማይባል ፣ ምንም ዓይነት ድካመት የሌለበት ኃያል ሁሉን የሚያውቅ የጥበባት መዝገብ ስለሆነ ጥበብን ያጣ ቢኖር ለሁሉም በልግሥና መስጠት የሚችለውን እግዚአብሔርን በጸሎት ይጠይቅ" ተብሎ ተጽፎአል ። (ያዕ 1.5)

ቄስ መክብብ አጥናው

# የጤና ዐምድ

## ጤናችን

ሥጋዊ አካልን ከበሽታ ጀርሞች ጠብቆ ሙሉ ጤነኛ በመሆን የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስና የክብሩ ማኅደር ለማድረግ እግዚአብሔር በአምሳሉ የፈጠረልን ሰውነታችን በጤና የተሞላ እንዲሆን መንከባከብ ያስፈልገናል ። በእራሳችን የጤና አጠባበቅ ጉድለት ምክንያት በሰውነታችን ላይ ወይም ውስጥ በሽታ የሚያገኘን ጥቂቶቻችን እንደ ምንለው እግዚአብሔር ከሰማይ ልኮብን ሳይሆን በአኗኗራችን ከምናደርገው ስህተት መሆኑን መዘንጋት የለበትም ።

እግዚአብሔር የሠራውን ሰውነታችንን እንድንከባከበው የሚገባውንም እንድናደርግለት በሚቻለን ሁሉ ከሚጎዳውና ከሚያረክሰው ነገር እንድንጠብቀው ያዘናል ።

የጤናችን ይዞታ በመጀመሪያ በአለባበሳችን ፣ በአመጋገባችንና ከመጠጣች የተመሠረተ ነው ለማለት ይቻላል ። እነዚህ የጤና መሠረቶች ናቸው ያልናቸውን እያንዳንዳቸውን ብንመለከት በአለባበሳችን በኩል በሚያጠብቅ ልብስ ሰውነታችንን ብንወጥረው በሰውነታችን ውስጥ የሚተላለፈው ደም መስናክል ሊኖርበት ይችላል የአለባበሳችን ሁኔታ የውስጥ ሰውነታችን የተፈጥሮ ይዞታ እንዲጠበቅ ሆኖ መለበስ አለበት ያለዚያ ሊተላለፍ የሚገባው ደም በተለበሰው ጠባብ ልብስ ምክንያት ደሙ ወደዋናው ክፍል እንዲጠራቀም ያስገድደዋል በዚህ ምክንያት የተመለሰው ደም የራስምታት ፣ ሳል ፣ የልብ ትርታ መፍጠሩን ፣ ወይም የምግብ አለመስራጨትን ያስከትላል ይህ በጠባብ አለባበስ ምክንያት የጤናችንን ሁከት የሚያመጣ ሲሆን የአለባበስ ወቅቶችንም ያለ መጠበቅ የብርዱን በሙቀት ፣ የሙቀቱን በብርድ ሰዓት መልበስም ለጤናችን ከማይስማሙት ወይም ጤነኛ የነበረውን ሰውነታችንን ለበሽታ ከሚያጋልጡት ዋንኛዎቹ ናቸው ።

በአመጋገባችን የሚመጣውንም የጤና ጉድለት ብንመለከት ለሰውነት መገንቢያ የሚያስፈልጉት ነገሮች በበለጠ የሚገኙባቸውም ምግቦች መመረጥ አለባቸው የእያንዳንዱ የሰውነታችን እንቅስቃሴ አንጎልና አጥንቶች ሁሉ ምግብ ያሻቸዋል ለዚህ በምግብ እረዳትነት ለሚንቀሳቀሱ የሰውነታችን ክፍሎች የተሻለ ምግብ ለማወቅ ምን እንደሆነ ከተፈለገ እግዚአብሔር በመጀመሪያ ለሰዎች የሰጠውን የምግብ ዓይነት ማወቅ ያስፈልጋል ። ሰውን የፈጠረና ፍላጎቱንም የሚያውቅ አምላክ ለአዳም የሚበላውን ምግብ ዓይነት ወሰነለት ።

"እነሆ መብል ይሆናችሁ ዘንድ ዛሬ በእርሱ ያለውን ሐመልማል ሁሉ የዛፍንም ፍሬ የሚያፈራውን ዘር ያለውንም ዛፍ ሁሉ ሰጠኋችሁ ዘፍ 6 ፣ 9"

በዚህ ላይ እግዚአብሔር የመረጠልን ምግብ ጥራጥሬ ፣ እህል ፣ ፍራፍሬ ሥርና ቅጠላቅጠል (አትክልት) ናቸው የተፈጥሮ ጣዕማቸው ሳይጠፋና ብዙ ነገር ሳይጨመርባቸው ከተዘጋጁ እነዚህ ምግቦች የምግብ ፍላጎታችንን ለማሟላትና ሙሉ ጤንነትን ለመስጠት ይችላሉ ብዙ ነገር ከተጨመረባቸውና በጣም ከሚጣፍጡት ሰው ሠራሽ ምግቦች የበለጠ ኃይልና ጥንካሬ ይገኝባቸዋል ። ታዲያ እነዚህን ምግቦች ለወቅቱ ለዓየሩ ሁኔታና ለሥራችን ተስማሚ ሆነው ተዘጋጅተው ከቀረቡልን ማለት ነው ። በተሲያየ ሰዓት ልንመገባቸው የሚገቡን ምግቦች በአንድ ጊዜ መውሰድ ትክክለኛ አመጋገብ አይደለምና ሊጎዳን ይችላል ልዩ ልዩ ሥራ ለሚሠሩ ሰዎች የሚዘጋጀው ከባድ ሥራ ለማይሠሩት ወይም በቅምጥ ለሚሠሩት ወይም የአእምሮ ሥራ ለሚሠሩት ሰዎች ተስማሚ ሊሆን አይችልም ወይም የሕጻናት ምግብ ለአዋቂ በቂ አይደለም የምግባችን አዘገጃጀት ተመጣጣኝነት ከሌለው ለጤናችን ምቹ አይሆንም ከሥነ ፍጥረት የተገኙትን ምግቦች አዘጋጅቶ አመቻችቶ ማቅረብ የእኛ ፋንታ ነው እግዚአብሔር እንድንመገብ ከፈቀደልን ፍራፍሬዎችና አትክልቶች የሚገኘውን የሚተካ የለም የአበላላችንን ጊዜዎች ካስተካከልን ማለት ነው ።

ምግብን በበቂ ሁኔታ ማዘጋጀት ወይም የተዘጋጀ ምግብ መኖር ብቻ ካለአመጋገብ ዘዴ ብቻውን በቂ አይሆንም ጥሩና ለጤና ተስማሚ የሆነው ምግብ በአመጋገብ ያለመስተካከል ብቻ ለጤና ጐጂ መሆኑ የጤና ጥበቃ ክፍል በየጊዜው በመገናኛ መሣሪያዎች ይመክራል የመኝታ ሰዓት ሲደርስ መመገብ ወይም በምግብ ሰዓት መተኛት በችኰላ መመገብ ፣ ከምግብ በኋላ ዕረፍት አለማድረግ ፣ በጣም የሞቀ ወይም የጋለ ምግብ ከእሳት እንደወጣ ወይም በጣም የቀዘቀዘውን ከፍሪጅ አውጥቶ መመገብ ፣ ያለልክ ሆድ በቁንጣን እስኪያዝ መብላት በድካም ወይም በብስጭት ጊዜ መብላት ከምግብ በፊት ጣፋጭነት ያላቸውን ነገሮች መብላትና በጠቅላላው የአመ

ወደ ገጽ ፳፱ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org



ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤ ክርስቲያን ሊቃውንት እያጠኑ ታሪካቸውን የሚያቀርቡልን አለቃ ዐምደ ጽዮን እኒህ ናቸው ።

## ሊቃውንቶቻችን

አራት ዓይና ጐሹ

የአራቱ ጉባኤያት ማለት የብሉያት ፣ የሐዲሳት የመጻሕፍተ ሊቃውንትና የመጻሕፍተ መነኮሳት ሊቅ የነበሩት አራት ዓይና ጐሹ በጐጃም ክፍለ ሀገር በደብረ ማርቆስ አውራጃ የውሽ ሚካኤል በሚባለው ደብር በ1781 ዓ.ም. አካባቢ ተወለዱ ።

የአራቱ ጉባያት ሊቅ ለመባል ያበቃቸውን የተሟላ ሞያ በየረድፉ ካጠናቀቁ በኋላ ስማንያየሚሆኑ ስመጥሩዎች ኢትዮጵያውያን ሊቃውንትን በትምህርት ወልደዋል ።

ከተማሪዎቻቸውም ዋና ዋናዎቹ ፣

1. መምህር አካለ ወልድ 2. መምህር ሰው አገኘሁ 3. መምህር ገብረ ኤልያስ 4. መልአከ መልአክ ኃይሉ 5. አለቃ ተክለጽዮን 6. አለቃ ሥነ ጊዮርጊስ 7.መምህር ክፍለ ጊዮርጊስ 8.መምህር ፀበሉ የመሳሰሉት ሁሉ እንደነበሩ ከትውልድ ወደትውልድ ሲያስተጋባ የኖረው ታሪካቸው ያረጋግጣል ።

አራት ዓይና ጐሹ ጉባኤ ዘርግተው ሲያስተምሩ የነበረው በዚያው በአገራቸው በጐጃም ክፍለ ሀገር በሞጣ ቅዱስ ጊዮርጊስ ደብር እንደነበረና አስተማሪያቸውም መኖኝ ገብረ ሕይወት የተባሉት ሊቅ መሆናቸው ታውቋል ።

### አራት ዓይና የተባሉበት ምክንያት

ጐሹ በሚለው ስመ ተፀውዖ ላይ አራት ዓይና የሚል ቅጽል የተጨመረላቸው ከላይ እንደተመለከተው የአራቱ ጉባኤያት ሊቅ በመሆናቸው እንዲሁም ይህ ዓይነቱ ስም አጠራር እንደባህል ትቆጥሮ አራቱን ጉባኤያት ላወቀ ሊቅ ሲሰጥ በመቆየቱ እንደነበረ የጥንቱን ወግና ሥነ ሥርዓታዊ ታሪክ የሚከታተሉ የምርምር ሰዎች ያስረዳሉ ።

ሆኖም በዚህ ዓይነቱ የታሪክና የባህል ሐዲት ላይ ተመሥርታና መዋቅሮቿን አጠናክራ ለረጅም ጊዜ የኖረችው ቤተ ክርስቲያናችን ባሁኑ ጊዜ ይኸንን የመሰለ ከፍተኛ የሆነ የሊቅነት ስም የምትሰጠው ወይም የምታወርሰው ምሁር ባለማግኘትዋ እጅግ አድርጎ የሚያሳዝንነው ።

ይሁን እንጂ ለምርምር ለዕውቀትና ለሥራ የተሰለፈው የዘመኑ ትውልድ በትምህርት የሚገኘው ይህ ከፍተኛ ስም እንዳይዘለውና በታሪክ እንዳይከሰስ ወይም እንዳይወቀስ ተገቢ ጥረት የሚያደርግ መሆኑን በማስመልከት ቤተ ክርስቲያን አራት ዓይና ከሚያሰኘው ከሊቃውንት የስም መድረክ ላይ የምታቆማቸውን ሰዎች ተስፋ ባለመቁረጥ ትጠባበቃለች ።

### አራት ዓይና ጐሹን ሹመት ፈለጋቸው እንጂ አልፈለጉትም

ከላይ እንደተመለከተው ሁሉ አራት ዓይና ጐሹ መጻሕፍትን በመመልከት በምርምርና በማስተማር ላይ ሳሉ ጉባኤ ዘርግተው ያስተምሩበት የነበረው የሞጣ ቅዱስ ጊዮርጊስ ደብር አለቅነት እንዲሰጣቸው ሁለት ሰዎች ለእኔ ለእኔ በማለት ለደጃዝማች ተድላ ጓሉ አመለከቱ ።

ደጃዝማችም አመልካቹ ምንም ወዳጆቻቸው ቢሆኑ "ከመጠምጠም መማር ይቅደም" የሚለውን የአባቶች ወግና ሥርዓት በመከተል ሁላችሁ በትምህርት ተፈታትናችሁ በሙያው የበለጠ ሹመቱን ይውሰድ " ስለአሉ ሹመቱን ጠያቂዎቹ በሙያማ ከሆነ ሁለታችንንም የሚበልጥ ጐሹ የተባለ ሊቅ አለና ለእኛ ቀርቶብን ለእሱ ይሰጠው ብለው በእውነት ስለ እውነት ጠቆሙ ።

በዚህም ጊዜ ደጃዝማች ተድላ፡- ጐሹ የሚገኘው ወዴት ነው? ብለው ቢጠይቋቸው ሞጣ መጻሕፍት ቤት (ትምህርት ቤት) ስለአሏቸው የሹመቱን ደብዳቤና ሽልማቱን ለአራት ዓይና ጐሹ ወደዚያው ወደ ትምህርት ቤታቸው ድረስ ልከውላቸዋል በዚህም ጊዜ የደብሩ ካህናትና የአካባቢው ምእመናንም በደስታ ተቀብለዋቸዋል ።

አራት ዓይና ጐሹ የደብር አስተዳዳሪነቱን ተግባር ጉባኤ ዘርግቶ ከማስተማር ጋር አጣምረው በማከናወን ለሞጣ ቅዱስ ጊዮርጊስ ደብር ካህናትና ለአውራጃው ምእመናን የአራት ዓይናቸውን ብርሃን አካፍለውታል ።

### አራት ዓይና ጐሹ የትምህርት ጉባኤ ያቸውን ይንከባከቡታል

ደጃደጃዝማች ተድላ ጓሉ የሞጣ ቅዱስ ጊዮርጊስን ደብር በማስተዳደርና ለብዙ[...] ሙርት ጉባኤ ዘርግቶ በማስተማር የሚያደርጉትን ከፍተኛ የሥራ አስተዋጽኦ ከገመገሙ በኋላ በፍሬያማ ውጤታቸው እጅግ አድርገው ስለ ተደሰቱ ለእርሻ የሚያገለግሉ በሬዎች ፣ ወተትን የሚሰጡ ላሞች መርጠውና አስመርጠው ቢልኩላቸው ሊቁ የጉባኤያቸውን መስፋፋትና የተማሪዎቻቸውን ቁጥር ብዛት እንደ ዓይን ብለን ለመጠበቅ እንጂ ለዚህ ዓለም ገንዘብ የማይስገበገቡለት ስለሆነ በሮቹንና ላሞቹን በሙሉ መልሰው ወደ ደጃዝማች ወስደው ከምስጋና ጋር አልፈልግምና ይቀበሉኝ ብለዋቸዋል ።

ደጃዝማችም ስጡኝ በማለት ፋንታ የሰጡትን እንደገና ይቀበሉኝ የሚል ሰው ያጋጠማቸው ለመጀመሪያ ጊዜ መሆኑን ገልጸውና በዚሁ ሁኔታ ተደንቀው ስለምንድን ነው ስጦታዬን የመለሱት? ብለው ቢጠይቋቸው ለእኔ ሀብቴ ንብረቴ የትምህርት ጉባኤዬ ነው ፣ ከብቶቹን ተማሪዎቼ እንዳይጠብቋቸው ጉባኤው ይፈታብኛልና አልፈልግም ስለአሏቸው በጥበቃው ሥራ የሚረዳቸው ሰው ሰጥተው ከብቶቹን መልሰው እንዲወስዱ አድርገዋል ።

አራት ዓይና ጐሹ ግን ስጦታውን በፍጹም ላለመፈለግ ያደረጉት እንጂ በከብቶቹ ጠባቂ ችግር ብቻ ይህን ለማድረግ እንዳልወሰኑ ከታሪክ ተከታታዮች ይነገራል ። ይኸም ሁኔታ የኢትዮጵያ ሊቃውንት ከሚደነቁበት ባህላዊ ይዞታ ዋናው ወይም የመጀመሪያው ነው ቢባል ይቻላል።

### የደብረ ታቦር ከፍተኛ ጉባኤ

ዓፄ ቴዎድሮስ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በየጊዜው ከግብፅ ጳጳሳትን በማስመጣቷና ተወላጆቿ ለዚህ ሐዋርያዊ ዕድገት ባለመድረሳቸው በጣም ያዝኑ ነበርና ጳጳሳት ከግብፅ ወደ ኢትዮጵያ መምጣታቸው ቀርቶ ኢትዮጵያውያን የሚሾሙበት መንገድ እንዲከፈትና ይህም በዝርዝር ተጠንቶ እንዲወሰን በጎንደር ክፍለ ሀገር በደብረ ታቦር ከተማ ከፍተኛ የሆነ የሊቃውንት ጉባኤ እንዲደረግ ትእዛዝ ሰጡ ።

በዚህም ስብሰባ ላይ ከሊቃውንቱ አንደኛ የነበሩት አራት ዓይና ጐሹ እንዲገኙ ተደርጎ ነበርና ሊቃውንቱ ስለዚሁ ጉዳይ በሞቀና በደመቀ ክርክር ላይ ሳሉ አራት ዓይና ለክርክሩ በር የሚከፍትና ለውይይት የሚሆን ሥላሴ ቅኔ ለጉባኤው አቅርበዋል ።

በግእዝ ከቀረበውም ቅኔ ፍሬ ነገር በከፊል በአማርኛ


"ቁስጥንጥንያ ምንድነች?
ቁስጥንጥንያማ ኢትዮጵያ ነች
ኒቅያም ደብረታቦር ነች" ይል ነበር ።

የጉባኤውን የአሳብ ዝንባሌና መንፈስ ተከትሎ በቀረበው በዚህ ቅኔ ዓፄ ቴዎድሮስ እንዲሁም ሊቃውንቱ በጣም ተደንቀዋል ከዚህም ላይ ልንገልጸው የሚገባን አንድ ነገር አለ ።

## መስቀሉና ሕይወታችን

በጠራ ሰማይ ላይ ሲያሽበርቁ ያደሩ ከዋክብት ለቀኑ ብርሃን ቦታቸውን ለመልቀቅ በመጣደፍ ላይ ናቸው ። ቀዝቀዝ ያለ አየር ይነፍሳል ። ሰማዩ አልፎ አልፎ ደርፎ ሲንፀባረቅ የሚሰጠው የብርሃን ጨረር ልዩ ትርዒት ነበር ። ይህም አተኩሮ ለተመለከተው የሚያሳየው የተፈጥሮ ውበት እጅግ የሚያስደንቅ መሆኑን ነው ።

ዕለቱ ከሳምንቱ ስድስተኛ ቀን (ዓርብ)



ክርስቶስ የሾህ አክሊል እንደ አደረገ

መና ጥሎበት ይታያል ። ጊዜው ገና ጧት ነው ፤ ጸሐይዋ የወጣች ቢሆንም ሙቀቷ እስከዚህም አልበረታም ፤ ደም እንደረጨት ሁሉ ደም መስላ ለጉዞ የተዘጋጀች ትመስላለች ። የብርድ ወራት በመሆኑ ሰው ሁሉ ፀሐይዋ እስክትሞቅ ከቤቱ ለመውጣት አይደፍርም ። ይህ ዕለት ግን ከሌሎች የተለየ ነበር ። በብርድ ምክንያት አርፍዶ ይነሣ የነበረው ሁሉ በዚህ ዕለት ማልዶ ተነሥቶ አል ። የማለዳው የፀሐይ ጨረር በኢየሩሳሌም ከተማ ባሉ ታላላቅ ሕንፃዎች ላይ አሲሆን ያለወትሮው ብዙ ሰው ከገጠሩ አካባቢ ሳይቀር ወደ ከተማው ሲጎርፍ ይታያል። ምክንያቱም በዚሁ በኢየሩሳሌም ከተማ ትናንትናውን ምሽት አንድ አስደናቂ ወሬ ተሰምቶ ነበር ። ይኸውም የአይሁድን ወግና ልማድ የሚሽር ያረጀና ያፈጀ ሥርዓት የ

ሚያወግዝ ፣ በአዲስ ትምህርቱ ኢየሩሳሌምን ይገለባብጣል የተባለው የአንድ ጎልማሳ መምህር መያዝ ነበር ። ይህ ሰው ከሦስት ዓመታት በፊት ጀምሮ ከካህናት አለቆችና ከፈሪሳውያን (የአይሁድ ሊቃውንት) የከረረ ተቃውሞ ሲደርስበት መቆየቱን ሁሉም ሰምተዋል ። በሮማው የቅኝ አገዛዝ ሥር ወድቀው የነበሩ የአይሁድ ሕዝቦች ከዚህ ምድራዊ የጭቆና አገዛዝ ነፃ ያወጣናል ፤ መንግሥታችንን ይመልሳል ብለው ተስፋ ጥለውበታል ። ስለዚህም የዚህ ሰው ዝና ከተሰማ ወዲህ ድርጊቱን በቅርብ ሲከታተሉ ቆይተዋል ። ሆኖም ዛሬ ይህ መምህር በቅናትና በምቀኝነት በተነሣሡበት የአይሁድ መሪዎች እጅ አልፎ መሰጠቱ ይነገራል ፤ ስለዚህ ብዙዎች የመጨረሻውን ውጤት ለማየት ጉጉት አድሮባቸው ነበር ። በምሽቱ ጊዜ ከተያዘ በኋላ በዚያች ሌሊት በብዙ ግርፋት ሲመረመር ማደሩ ከማለዳ ጀምሮ ወሬው ተዛምቶአል ። ፍርዱም በዚሁ ዕለት እንደሚፈረድ ከፍርድ ሸንጐው አካባቢ ይወራል ። ስለዚህ ሁሉም ይህን ወሬ በመስማቱ የሚሰጠውን ፍርድ ለመስማትና አፈጻጸሙን ለመመልከት ወደከተማይቱ አደባባይ በመጉረፍ ላይ ይገኛል ።

ልክ ከጧቱ ሦስት ሰዓት ሲሆን ከአገረ ገዢው ከጲላጦስ ግቢ አካባቢ ብዙ ሰው እየተንጫጫና እየተተራመሰ ሲወጣ ታየ ። ከሕዝቡም መሐል አንድ እሥረኛ በወታደሮች ታጅቦ ሲመጣ ይታያል ። እሥረኛው የለበሰው ልብስ ከመቦጫጨቁም በላይ ሁለመናው በደም ተበክሏል ። በጣም የተጐሳቆለ መልክ ይታይበታል ። ("መልክና ውበት የለውም ፡- ባየነውም ጊዜ እንወደው ዘንድ ደም ግባት የለውም" ኢሳ. 53፡2 ) ከሚንጫጫው ሕዝብ"...ሞት ተፈርዶበታል ፤ ሊሰቀል ነው ፤ ሊሰቀል ነው" የሚል ድምፅ ደጋግሞ ተሰማ ።

ወዲያው ብዙ ሰዎች የተመሳቀለ ትልቅ ግንድ እንጨት እየጐተቱ አመጡ ። ይህንግንድ ያላንዳች ርኅራኄ በእሥረኛው ትከሻ ላይ ጫኑበት ። እሥረኛውም ያለማንገራገር እየወደቀ በመነሣት ግንዱን ተሸክሞ ጉዞውን ቀጠለ ። ("ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት ፣ በሸላቹም ፊት ዝም እንደሚል በግ ፣ እንዲሁ አፉን አልከፈተም ። በማስጨነቅና በፍርድ ተወሰደ ፤..." ኢሳ.53፡7-8)

ከርሱም ጋር የተፈረደባቸው ሁለት ክፉ አድራጊ ወንበዴዎች ነበሩ ። የሚሰቀልበትን ግንድ የተሸከመው እሥረኛ ግን ዘበኞቹ እያዳፉት ፣ ከኋላው የሚወርድበትን የጅራፍ ውርጅብኝ የስድብ ቃላት በዝምታ እየተቀበለ ይጓዛል ። በብዙ ሺህ የሚቆጠር ሕዝብ ተከትሎታል ። ግማሾቹ በተፈረደበ



www.ethiopianorthodox.org

[illegible]
ለትና ሲያለቅሱ ይታያል ። በተለይም አብ
ረውት የነበሩ ረዳቶቹ ሴቶችና ተማሪዎች
ስቅስቅ በማለት እያለቀሱ ተከትለውታል።

[illegible] ወታደሮቹ እም
ረኛውን አስቆሙ ፤ እንጨቱንም አሳረፋለ
ት ። ይህ ቦታ የፍርዱ ውሳኔ የሚፈጸምበት
ነበር ። ከተያዘባት ከትናንትናዋ ምሽት ጀ

አዎ! ልብወለድ አይደለም ፤ ተረትም አ
ይደለም ። ከዛሬ 1938 ዓመታት በፊት በኢ
የሩሳሌም የተፈጸመ እውነተኛና አስደናቂ
ታሪክ ነው ። ክርስቶስ በለሰው ልጅ ደኅን



ክርስቶስ መስቀሉን ተሸክሞ ወደ ቀራንዮ ሲሄድ ሴቶች ያለቅሱ ነበር ።

ከብዙ ድካም በኋላ ቀራንዮ (ጎልጎታ) ወ
ደተባለች ኮረብታ ደረሱ ። አሁን የጧቱ
ውርጭ አልፎ ጤዛው ረግፎ ፀሐይዋ ከመ

ምሮ ያለዕረፍት ሲሰቃዩ ያደረውን ሰው ከ
ግንዱ ጋር እጆቹን በምስማር ቸነከሩት ።
በዚያችም በቀራንዮ ኮረብታ አናት ላይ ሰ

ነት በርግጥ ይህን ሁሉ መከራ ተቀብሏል።
በአይሁድ ካህናትና በሕዝቡ መሪዎች እጅ
ተሰቃይቷል በህጋቸው "በእንጨት የሚሰ



ቀል ሁሉ የተረገመ ነው" ቢባልም እንዳች
ም በደል አላደረገም ። ስለእኛ እርግማን ፈ
ንታ ገባ ፤ ኃጢአት የሌለበት አምላክ ሲሆን
እኛን ስለማዳን በደላችንን ሁሉ ተሸከመ።

ግማንም በታች ሆነ ። ስለዚህ መስቀሉ ና
ሕይወታችንን ብንመለከት የሚታወሱን ነ
ገሮች አሉ ። ለሕይወታችን ሕይወትን ለመ
መስጠት በደላችንን ሁሉ በመስቀል ላይ



መርዛሙ እባብ የነደፋቸው ሁሉ ወደ ናሱ እባብ ሲመለከቱ ይድኑ ነበር ።

ለተረገሙት የሚገባው የመስቀል ሞት ጽ
ዋ ለእርሱ የታዘዘ ሆነ ። ("ክርስቶስ ስለእ
ኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን።"
ገላ.3፥13 ) በመሠረቱ በአይሁድ ሕግ በመ
ስቀል የሚሞት ወንጀለኛና የተረገመ ሰው
ነበር ፤ ክርስቶስ የበረከት ምንጭ ሲሆን ፣
ስለ በደላችን እንደርጉም ሆነ ።


የሰው ሕይወት ከአዳም ውድቀት ጀምሮ
በኃጢአት ምክንያት ተበላሽቷል ። ሰው ለ
ፈጣሪው ባለመታዘዙ ከእርሱ ተለየ ፤ ከእር

ተሸከመ በመስቀሉ እርግማናችንን አስወ
ግዶ ለሕይወታችን ደስታና ሰላምን ሰጠን
ስለዚህም ሥቃዩ ደስታችን ፣ መስቀሉ ፈ
ውሳችን ፣ ሞቱ ሕይወታችን እንደሆነ እንረ
ዳለን ። ነቢዩ ኢሳይያስ በዘመኑ ገና ከ600
ዓመታት በኋላ ስለሚፈጸመው የክርስቶስ
መከራ መንፈስ ቅዱስ ገልጾለት እንዲህ ሲ
ል ጽፏል ። "በእውነት ደዌያችንን ተቀበ
ለ ሕማማችንንም ተሸክሞአል ፣ እኛ ግን
እንደ ተመታ በእግዚአብሔርም እንደ ተቀ

ሠፈ እንደተቸገረም ቆጠርነው ። እርሱ ግን
ስለ መተላለፋችን ቆሰለ ፣ ስለ በደላችንም
ደቀቀ ፣ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ
ላይ ነበረ ፣ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን
እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠ
ፋን ፣ ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ
አዘነበለ ፤ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደ
ል በእርሱ ላይ አኖረ ። ...." (ኢሳ.53፥4-
7)
አዎ! ይህ ቅዱስ የእግዚአብሔር በግ ነፍሳ
ችንን ያስጨንቅ የነበረውን የሕይወት በሽ
ታችንን ተሸክሞ በመስቀል ላይ ተሠዋ ።
ከአዳም ውድቀት ጀምሮ በሕይወታችን ሥ
ር ሰድዶ የነበረውን የኃጢአት ደዌያችንን
ሁሉ ተቀበለ ። በበደል ምክንያት ከጸጋ ሕ
ይወት ወጥቶ የተጐሳቆለውን ሰው ለማዳን
ሲል በሰው እጅ ቆሰለ ። መድኃኑ በመስቀ
ል ላይ ሆኖ ሲታይ ሰው ፊቱን እንደሚሰው
ርበት ነበር ፤ እስከፊ በደላችንን ተሸክሟል
ና ።

ይህንኑ የኢሳይያስን ቃል ጠቅሶ ሐዋር
ያው ጴጥሮስ እንዳለው ፦ ክርስቶስ በሥጋ
ው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ
እርሱ ተገርፎ በመቁሰሉ እኛ ከነፍሳችን ቁ
ስል ተፈውሰናል ። ከበደላችን የተነሣ ከአ
ምላካችን ተለይተን እንደ በጎች ተቅበዝብ
ዘን ነበር ፣ አሁን ግን በክርስቶስ የመስቀል
ሞት ወደ ነፍሳችን ጠባቂ ተመልሰናል ።
(1ኛ ጴጥ.2፥24) በመካከል የነበረውን የጥ
ል ግድግዳ ማለት የኃጢአት ተራራ በመስ
ቀሉ አፍርሶልናልና ።

መስቀሉንና ሕይወታችንን ስናስብ የኃ
ጢአት ዕዳ በክርስቶስ ሞት እንደተከፈለል



ወደ ተሰቀለው ክርስቶስ በእምነት የሚመለከቱ ከኃጢአታቸው ይድናሉ ።



www.ethiopianorthodox.org

ን እናስተውል ይሆን? ማንም ሊፈጽመው ያልቻለውን እርሱ በመስቀሉ ሞት ሁሉን ፈጽሟል ። በሞቱ ሞትን ድል ነሥቶ ሕይወትን ሰጥቶናል ። ዛሬ ሁላችን ወደ መስቀሉ ዘወር ብለን በእምነት ዓይን ብንቃኘው ሰውን ወዳጅ አምላክ የፈጸመልንን ታላቅ ጸጋ እንመለከታለን ። በደላችንም ሁሉ በቀራንዮ ኮረብታ በእርሱ ላይ ተጭኖ እናያለን ። በዚህ ጊዜ ዕዳችን እንደተከፈለልን እንረዳለን ፣ እንገነዘባለንም ።

መድኅን ክርስቶስ በመስቀል ከመሠዋቱ በፊት አስቀድሞ ስለራሱ ሲናገር፡- "ሙሴም በምድረ በዳ እባብን እንደ ሰቀለ እንዲሁ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ይሰቀል ዘንድ ይገባዋል ።" (ዮሐ.3፣14.15) ሲል የመስቀሉን ነገር ተናግሮአል ወደ ኋላ መለስ ብለን ታሪክ ብናስታውስ ሕዝበ እሥራኤል በሲና ምድረ በዳ በነበሩ ጊዜ እግዚአብሔርን በመበደላቸው በእባቦች ተነድፈው ተሰቃዩ ። ሙሴም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና ትዕዛዝ የናስ እባብ ሠርቶ በእንጨት ላይ ሰቀለ ። በእባብ የተነደፈ በሽተኛ ሁሉ የተሰቀለውን እባብ ሲያይ ወዲያው ዳነ ። ለክርስቶስ መስቀል ምሳሌ ነው ። ያንጊዜ እሥራኤላውያን የተሰቀለውን እባብ በመመልከታቸው ብቻ ከደዌ ሥጋ ተፈወሱ ። እኛም ዛሬ በእዝነ ልቡና ቃሉን አድምጠን ፣ በዓይነ ሕሊና የቀራንዮን በግ በመስቀል ላይ ብናይ ወዲያዉኑ ከደዌ ነፍስ እንፈወሳለን ። ይህም ብቻ አይደለም በመስቀል የተሠዋውን መድኃኒት ክርስቶስን በእምነት ብንቀበል በሕይወት እንኖራለን ።

ወገኖቼ ሁላችን ሕይወታችንን ብንመረምር በበደል ረክሰናል ፣ በኃጢአት መርዝ ተነድፈናል ። የተነደፈ ሁሉ መርዙ በደም ሥር ወደልቡ ከደረሰ ያለው ዕድል ሞት ብቻ ነው ። ታዲያ በኃጢአት የተነደፍን ሁላችን በሕይወት ለመኖር እንፈልግ ምን? እንግዲያውስ መስቀሉን እንመልከት "የተነደፈውም ሁሉ ሲያይ በሕይወት ይኖራል" (ዘኁል. 21፡8) እንደተባለው የኃጢአትን መርዝ የሚያጠፋ መድኃኒት በመስቀል ላይ ተሰቅሏል ። በእምነት እንየው ፣ በሕይወትም እንኖራለን ።

የክርስቶስ መስቀል እንዲሁ በአጋጣሚ የሆነ አይደለም ፣ ለሕይወታችን ትርጉምና ዓላማ አለው ። ትርጉሙ መከራውንና ሕማሙን ፣ ዓላማው መዳናችን መሆኑን ያስረዳል ።

ሐዋርያው ጳውሎስ፡- "ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ" (ገላ 6፣14) እንዳለው መስቀሉ ለሕይወታችን መመኪያ ፣ ለድካማችን ኃይል ነውና ሕይወት ባገኘንበት መስቀል እንመካ ።

እንግዲህም መስቀሉን ለነፍሳችን መድኃኒት ለሕይወታችን ዘላለማዊ ሕይወትን ሰጭ መሆኑን ተገንዝበን በእምነት ወደ እርሱ እንቅረብ ።

ተስፋዬ ረጋሣ

## ሊቃውንቶቻችን

ከገጽ ፲፭ የዞረ

ይኸውም በመጀመሪያ በአንድ ቋንቋ የተነገረ ቃል ወደሁለተኛ ቋንቋ ሲተረጐም ሙሉ የሆነ አቀማመጡን ወይም የመደነቅ ስሜቱን ይዞ ለመተላለፍ እንደማይችል ሁሉ ግዕዝን ያልተከታተሉ አንዳንድ ሰዎች እንዳይቸገሩ በመገምገም የሲቁን ግዕዛዊ ቅኔ በአማርኛ ስናስቀምጥ ከዚህ በላይ የተገለጸው ሁኔታ እንደሚመለከተን የዘነጋን አለመሆኑን ነው ።

ዜና ዕረፍታቸው

አራት ዓይና ጐሹ ከትምህርት ዓለም ወደማስተማርና ወደደብር አስተዳደር ተዛውረው ብዙዎች ደቀ መዛሙርትን በትምህርት እየኰተኰቱ በመንፈስ ካሳደጉና የምእመናንን ልቡና በምርምር በሃይማኖት ካነፁ በኋላ ሰው ሆኖ ከሞት የሚቀር የለምና በ1860 ዓ.ም. አርፈዋል ። በዚህ ዓለም የኖሩበት ዘመን 80 ዓመት ነው ።

አለቃ ዐምደ ጽዮን ተሰማ

## የጤና ዓምድ

ከገጽ ፲፯ የዞረ

ጋገብ ሁኔታዎችን ያለማስተካከል የምግብ ፍላጐታችን (አፐታይት) እንዲቀነስ በማድረግ የተመገብነው ምግብ ለሰውነታችን ጠቃሚ ከመሆን ይልቅ ለጤናችን ሁከትን ይፈጥራል ይህም የጨጓራ በሽታን ያለአንዳች ጥርጥር ያስከትልብናል ። በዚህም የሚኖረን የምግብ ፍላጎት ወይም በሙሉ ከምንመገባቸው ምግቦች ለመቀነስ እንገደዳለን አሁን በበሽታ ከመያዛችን ም ሌላ የተሟላ ምግብን ለመመገብ እንድንችል እንከለከላለን በአንድ በሽታ ምክንያት የምንተወው ምግብ ለሙሉ ጤናችንም ጭምር ጠንቅ ይሆናል የተሟላ ምግብ አላገኘንም እና ነው ። ልንመገብ የሚገባን ምግብ እያማረን እንድንተወው በሽታችን ያስገድደናልና እንተወዋለን በዚህ የጤና ሁከት ድካምና ቀጥሎም ወደሚመጣው ሞት እንደርሳለን ።

መጠጣችንንም ከምግብ ለይተን እንተወውም ከምግባችን ጋር ልንጠጣው የሚያስፈልገን ውሃ ወይም ለስላሳ መጠጥ እንደሎሚ ጭማቂና (ጁስ) ለጤናችን ተስማሚነታቸው ከአልኰል ነክ መጠጦች ይበልጣሉ አልኰልነት ያላቸውን መጠጦች ከምግብ በፊትም ሆነ በኋላ መውሰድ ተስማሚነታቸው እምብዛም ነው እንደዚሁ ሻይና ቡና እንደ አልኰል እንኳ ያለ ኃይል ባይኖራቸውም በብዛት ከተወሰዱ ልብ ድካምን ያመጣሉ ። ይኸውም ለጊዜው የሰውነትን መነቃቃት ከቀጠሉ በኋላ ወደድካምና ደጋግሞ ወደ መጠጣት ያደርሳሉ ይኸም ልምድን ስለሚያመጣ በሚቻለን መጠን ሁሉ ምግባችንንም ሆነ መጠጣችንን በልምድ ላይ ብቻ የተመረኰዘ እንዳይሆኑ መጠንቀቅ ለጤናችን ይበጃል ከላይ እንደተጠቀሰው አለባበስና አመጋገብ የጤናችን መሠረትና ዋልታ መሆኑን ተገንዝበን ብንጠነቀቅ ጤናችንን ያለብዙ ገንዘብና ድካም መጠበቅ እንችላለን በዚህም ሰውነታችንን ያለአንዳች ጉድለት እስከሕይወታችን ፍጻሜ እንጠብቀዋለን ።

ጤናችን ሲጐድል የእኛ ያለመጠንቀቅ መሆኑን ባለመረዳት የምናማርረውን እግዚአብሔርን ልናመሰግነው እንችላለን ማለት ነው ።

ንብረት አበበ



# የሴቶች ዐምድ

## የሴቶች ሐዋርያነት

ጌታችን ኢየሱስ ለረዥም ዘመን በጭቆና ቀንበር ይኖሩ የነበሩትን ሴቶች ከ



ክርስቶስ ከተነሣ በኋላ ከሁሉ በፊት ያየችው መግደላዊት ማርያም ናት

ጭቆና አላቆ እኩልነታቸውን ያከበረ መሆኑ የማይታበል ሐቅ ቢሆንም ብዙ ሰዎች የሴቶች ሐዋርያነት ከትንሣኤው በኋላ እንጂ በፊት እንዳልነበር በማስመሰል የሚናገሩ ጥቂቶች አይደሉም ። ይሁን እንጂ ቅዱሳት መጻሕፍትን ስንመለከት ደግሞ ከትንሣኤው በፊት ብዙ ሴቶች ሐዋርያት እንደነበሩ ተጽፎ እናገኛለን ።

ለምሳሌ ሳምራዊቷን ሴት ብንወስድ ቁም ነገረኛ ወንጌላዊት እንደሆነች በመልእክቷ እናረጋግጣለን ። በሉቃስ ወንጌል በምእራፍ 8 ላይም ብዙ ሴቶች ይ



www.ethiopianorthodox.org

# ምን እንርዳዎ ?

**ይህ ዓምድ አንባቢዎች ችግራቸውን የሚገልጹበት ፣ ለችግራቸው መፍትሔ የሚሰጡበት ፣ ጥያቄና መልስ የሚያቀርቡበት ስለሆነ ምን እንርዳዎ ተብሎ ተሰይሟል ።**




አዘጋጅ ተስፋ ጥሩነህ
ስልክ ቍጥር 11-66-16
የፖ.ሣ.ቁ. 31-37
አዲስ አበባ


በትንሣኤ መጽሔት ምን እንርዳዎ አዘጋጅ
አዲስ አበባ

ቤተክርስቲያናችን ለተከታዮች ይህን የመሰለ ፕሮግራም በማዘጋጀቷ ደስ ብሎኛል ። ይህንንም ማለቴ አላማዋ ስለሆነ በመንፈስ የተቸገሩትን ሁሉ ማጽናናት ተገቢ መሆኑን በመገመት ነው ።

ከዚህ ቀጥዩ 1ኛ/ በሕይወቴ ውስጥ ያገኘሁትን የመንፈስ ለውጥ 2ኛ/ ስለ አክፍሎት 3ኛ/ አክፋይ እየተባለ ለዘመድ መስጠት ቤተ ክርስቲያን ታዛለች ወይ? እነዚህንም ዐበይት ጉዳዮች በዝርዝር አቀርባለሁ ።

ሀ/ በሕይወቴ ያገኘሁት የመንፈስ ለውጥ በጣም ወፍራም ነበርኩ ፣ ውፍረቴም ሌላውን ቀርቶ ራሴን አስቀይሞኝ ነበር ይህንንም ውፍረት ለመቀነስ ዘዴ እንዲሰጡኝ ለብዙ ሰዎች አማክሬ ነበር ነገር ግን አልተሳካልኝም በመጨረሻ ግን ለቤተ ሰቦቼ ንስሐ አባት ባማከራቸው ቤተ ክርስቲያን የምታዘውን ጾም ብትጾሚ አሳብሽ ይሟላልሻል አሉኝ እኔም አንድ ዓመት ያህል እንደ ጾምኩ ያ ሁሉ ውፍረት ተቀንሶ ሸንቃጣ ልጅ ሆንኩ ፎርሜም ቅርጼም የተስተካከለ ሆነልኝ ።

እንግዲህ የጾም ጥቅም በሥጋዬ በኩል ይህን ያህል የረዳኝ በመንፈሳዊ ሕይወቴም በኩል ፈጽሞ እንደሚጠቅመኝ አመንኩ ።

በዚህም ነገር ለሌሎች ምሳሌ ከመሆኔም ሌላ በቅርብ የሚያውቁኝ ጓደኞቼ ሁሉ በዚህ ዘዴ በመጠቀም ላይ ናቸው ።

ለ/ ስለ አክፍሎት በአካባቢዬ ያሉ አዛውንቶችና አሮጊቶች ሁዳዴን ከጾምሽ 2 ቀን ማክፈል አለብሽ አሉኝ ስለማክፈል ቤተ ክርስቲያን የምታዘው እንዳለ ብታስረዳኝ?

ሐ/ አክፋይ ለዘመዶቼ ለመውሰድ አስቤ ነበር ስለዚህ ጉዳይ ቤተ ክርስቲያን ደጋፊ ናት ወይ?

የመጽሔትዎ ተከታታይ
ወ/ሮ እማዋይሽ ፈጠነ

ወ/ሮ እማዋይሽ የላኩትን ደብዳቤ ተመልክቼዋለሁ በመጀመሪያ የመጽሔታችን አንባቢ በመሆንዎ ላመሰግን እወዳለሁ ከክርስቲያኖች የሚጠበቅ መንፈሳዊ ግዴታ ነውና ።

ከዚህም በኋላ በጾም በኩልም ጠቃሚ ውጤት ስላገኙ ለሌሎች ጥሩ ምሳሌ እንደ ሆኑና እንደሚሆኑም አልጠራጠርም ።

ስለ አክፍሎት መጽሐፍ ያዝዛል ወይ ? ስላሉት ፍትሐ ነገሥት ገጽ 152 ቁጥር 572 ''ዓርብንና ቅዳሜን ሁለቱን ቀኖች በአንድነት ጹሙአቸው የሚችል እስከ ሌሊት ዶሮ ጩኸት ድረስ ምንም ምን አይቅመስባቸው ሁለቱን ቀኖች በአንድነት መጾም ባይችል ግን የቅዳሜን ጾም ይጹም'' ይላል ።

ስለዚህ እርስዎም መጽሐፉ እንደሚያዘው ከቻሉ ዓርብና ቅዳሜን ጾመው ያክፍሉ፤ የማይችሉ ከሆነ ግን ቅዳሜ ስዑርን ብቻ እንዲጾሙ ተፈቅዷል ።

ሐ/ ለአክፋይ ስለ መውሰድ ቤተ ክርስቲያን ትፈቅዳለች ወይ? ስላሉት ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ምንም እንኳ ለበጐ ሥራ ተባባሪና ደጋፊ ብትሆንም አክፋይ ውሰዱ ብላ አታዝም ይሁን እንጂ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተከታዮች የሆኑ ሁሉ በፋሲካ በዓል ያገኙትን ሁሉ አብሮ መብላት አብሮ መጠጣት ተባብሮ የደስታው ተካፋይ መሆን ደስ ስለሚላቸው ለረጅም ጊዜ ወደው ሲሠሩበት ቆይተዋል ።

ስለዚህ ነው ለየዘመዶቻቸው አክፋይ ለመውሰድ የሚገደዱት፤

እኔ በበኩሌ የምሰጥዎ ምክር ቢኖር በአሁኑ ጊዜ በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ አደጋ ለተጐዱ ወገኖቻችን ፣ እንዲሁም በአድኀሪ ወራሪዎች ለተቃጠሉ አብያተ ክርስቲያናት ማቋቋሚያ በእርዳታ ስም ቢሰጡ የተሻለ ነው እላለሁ ።

ላላኩትና በገንዘባቸው ሳይቀር ያገለግሉት እንደነበር ቃሉ ይናገራል ።

በትንሣኤውም ጊዜ ሴቶች የመጀመሪያዎቹ ሐዋርያት እንደነበሩ ለማረጋገ ''ሂዱና ንገሩ'' ተብሎ የተነገራቸው ቅዱስ ቃል ብቻ በቂ ማስረጃ ሊሆን ይችላል ። እነርሱም እንሞታለን ብለው ምንንም ሳይፈሩ የክርስቶስን ትንሣኤ በአደባባይ ደፍረው ተናግረዋል ።

ይህም የሚያመለክተው ሴቶች በተሰለፉበት ሥራ ቆራጦችና ትጉሆች አገልጋዮች መሆናቸውንና ስለ ክርስቶስ ያላቸው ፍቅር እስከ ሞት ድረስ ብቻ ሳይሆን ስለ እርሱ ሞት እንኳን ቢሆን የማይፈሩ እውነተኞች ሐዋርያት መሆናቸውን ነው ።

ከትንሣኤውም በኋላ ሴቶች ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በጸሎትና ሐዋርያትንም በመምረጥ ጊዜ ተካፋዮች ነበሩ ። እንደዚሁም በሐዋ. ሥራ በም. 12 ቍ. 12 የመጀመሪያይቱን ቤተ ክርስቲያን መሥራቾች እንደሆኑ መጽሐፉ ያብራራል ።



# ወጣቶች ጋብቻን ለምን ይፈራሉ?

ጋብቻ ከቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት አንዱ መሆኑና ይህም ቅዱስ ጋብቻ ታላቅ ምስጢር እንደሆነ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በረጅሙ ይናገራል ።

ታላቁ ቅዱስ መጽሐፍም ''መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር ነው መኝታውም ንጹሕ ነው ይልና ጋብቻን ስለሚያፈርሱ ሰዎች ደግሞ ''ሴሰኞችንና አመንዝሮችን ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል'' ሲል ያስጠነቅቃል ።

አዎ ላልቀመሱት ማር እንደ እሬት መራር መስሎ ይታይ ይሆናል ሲቀምሱት ግን ማሩ ያው ጣፋጭ ማር ነው እንዲሁም ሁሉ በወንደላጤነትና በሴተ ላጤነት በየሥፍራው ወጥ ቀማሽ ከመሆን ይልቅ የዕረፍትና የደስታን ኑሮ ለማግኘት ጋብቻን መምረጥ ቀምሶም ማየቱ አስፈላጊ ነው ።

ቅዱስ መጽሐፍ ''ሰው ብቻውን ይኖር ዘንድ አይገባውም'' ይላል ታዲያ ይህን የመሰለ መመሪያ ሕግ እያለ ወጣቶች ጋብቻን እንዴት ሊፈሩ

---

ሴቶች ሐዋርያት ያላመኑትን በማስተማር እንዳሳሙኑ ትንቢት በመናገርና በዲቁና ሥራ ሳይቀር እንዳገለገሉ አሙን ነው ።

አንዳንድ ስለ ክርስትና እምነት ጠለቅ ያለ ትምህርትና እምነት የሌላቸው ሰዎች የክርስትና እምነት ሴቶችን የሚጨቁን በማስመሰል አንዳንድ ጥራዝ ነጠቅ ጥቅሶችን እየጠቃቀሱ ወጣት ሴቶች ከቤተ ክርስቲያን እንዲርቁ የሚያደርጉ ግለሰቦች አይጠፉም ።

ነገር ግን የተጠቀሱትን ጥቅሶች ስንመረምር የክርስትና እምነት ስለ ሰዎች ልጆች እኩልነት የሚናገርና የሚያንጸባርቅ ሃይማኖት ሆኖ እናገኘዋለን እንጂ ሴቶች እንዲጨቆኑ አያደርግም ስለዚህ በሃገርና በሃይማኖት ቀልድ የለምና ግለሰቦች ጥራዝ ነጠቅ አነጋገራቸውን እንዲያርሙ እንጠይቃለን ።

በተረፈ ሰውንና እግዚአብሔርን በሚያገናኘው መንገድ መራመድና ለሌሎቹም ቀናውን ጐዳና ማሳየት የሚኖርባቸው የወንዶች ሐዋርያት ብቻ ሳይሆኑ የሴቶች ሐዋርያትም እንደሆኑ በላይ ከሞላ ጐደል ከጠቆምናቸው ማስረጃዎች ልንረዳ እንችላለን እግዚአብሔር የሚመለከተው ልባችንን እንጂ ፆታችንን አይደለም ።

ስለዚህ ሥራችን አነጋገራችን አስተሳሰባችን ከክርስቶስ ሥርዓት ጋር የሚስማማ መሆን አለበት ክርስቶስ እንዲረዳን ከፈለግን ከጉድለታችን መታረም አለብን ። ቃሉ ''ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም'' ይላል እውነትም ያለ እርሱ ምንም ማድረግ አንችልም ። እንግዲያውስ እርሱን አማካሪያችን አድርገን ያለ ምንም የፆታ ልዩነት ከእርሱ በተማርነው መሠረት እውነተኞች ሐዋርያት እንሁን ።

ድንጋይና ጭቃ ቢቀጣጠሉ ታላቅ ቤት ረጅም ቅጥር ይሆናሉ እናንተም መሬታውያን ሰዎች እንደዚህ ብትረዳዱ ጥበባችሁና ኃይላችሁ ከሰማይ በደረሰ ተብሎ እንደተጻፈው ሁሉ እኛም ጥበባችንና ኃይላችን ከፍ ያለ እንዲሆን ወንድ ሴት ቄስ ዲያቆን ብለን ሳንለይ ሁላችንም የሚፈለግብንን ግዳጅ ከፈፀምን ለቤተ ክርስቲያናችን ኩራትና ብልጽግና ለሌላውም አርዓያ ልንሆን እንችላለን ።

የምሳሌ መጽሐፍ እንዲህ ይላል፦ እናንተ ሰነፎች ድንቁርናን ከማይመለስበት ሽጡት የሰነበተ እንደሆነ ሁልጊዜ ያው ይመስለዋልና ።

በዚህ ጥቅስ መሠረት ስንፍና ስንፍናችንን አይቶ ተንሰራርቶ እንዳይቀመጥ በሕብረት በፍቅር ያለ ነቀፌታ ያለ ፆታ ልዩነት ለመሥራት ተባብረን እንነሳ የሴቶች ሐዋርያነት ከትላንትና በስቲያ የተጀመረ ትላንትና የነበረ ዛሬ ያከተመ ሳይሆን ከክርስቶስ ልደት ጀምሮ በየጊዜው ብዙ የሴቶች ሐዋርያት እንደ ነበሩ መጽሐፉ ያስረዳል ። ዛሬም ቢሆን ሃሳባችንን በሙሉ ለእርሱ ብናስረክብ እግዚአብሔር በብዙ መንገድ ሊጠቀምብን እንደሚችል ማወቅ አለብን ። እግዚአብሔር ለሥራው የሚመርጣቸው ሰዎች ወንዶች ብቻ ወይንም ደግሞ አፈ ጮሌዎች የሆኑትን ሳይሆን ቃሌን በከናፍራቸው ላስተላልፍ እችላለሁን ? እኔን ሊወክሉ ከእኔ ለመማር ትሁታን ናቸውን? በማለት ስለሚጠይቅ የእርሱን ቃል በእውነት ተቀብለው እውነተኞች ሐዋርያት የሚሆኑትን ነው ።

ስለዚህም ራሱ ክርስቶስ ተገልፆ የተናገራቸውና ፍቅሩንም የገለጸላቸው ሴቶች በጊዜው የነበረውን የአይሁድን ቁጣ ሳይፈሩ ወንዶች ደቀ መዛሙርቱ ሳይሄዱ እነእርሱ ገስግሰው ሄደው ከመቃብሩ አጠገብ ተዘዋውረው ይፈልጉት ለነበሩትና በትህትና ከእርሱ ተምረው በእውነት ማስተላለፍ ለሚችሉት ሴቶች ሐዋርያት ነበር ።

በዚህም መሠረት በሃገራችን እናቶችም የእነርሱን ፈለግ በመከተል በሐዋርያነት በጉልበታቸው ፣ በገንዘባቸውና በሃሳባቸው ቤተ ክርስቲያንን ሲያገለግሉ ቆይተዋል አሁንም በማገልገል ላይ ናቸው ።

ለዚህም ማስረጃ ቢያስፈልግ በየ አብያተ ክርስቲያናቱ ዙሪያ በየጊዜው ጡዋፉን ፣ ዘቢቡን ፣ መባኡንና በጠቅላላ ለቤተ ክርስቲያኒቱ የሚያስፈልጋትን ሁሉ ይዘው የሚጐርፉት የሴቶችን ብዛት መመልከት ነው ።

እንግዲያውስ እኛም ወጣት ክርስቲያን ሴቶች የእናቶቻችንን አርዓያ በመከተል እውነተኞች ሐዋርያት ለመሆን በቃሉ የማናፍር ከሆነ ለክርስቲያን ሴቶች የውይይት ዓምድ እንዲሆን ታስቦ የሴቶች ዐምድ ተብሎ በዚሁ መጽሔት ስለተከፈተ ጥያቄአችንንም ሆነ ትምህርታችንን እየጻፍን ለዚህ ዐምድ አዘጋጅ እንድንልክ ተጋብዘናል ለእውነተኛውና ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ለተነሣው እግዚአብሔርም በቃሉ ሳናፍር እንደቀደሙት እናቶች በሐዋርያነት እንድናገለግለው ተጠርተናል ጥሪውን አክብረን ዛሬውኑ ለመገኘት እንዘጋጅ የዝግጅት ቀን ዛሬ እንጂ ነገ አይደለምና ።

ብርሃን ተድላ




www.ethiopianorthodox.org

## መብት ከግዴታ ጋር

ብዙ ሰዎች መብታችንን ተገፈፍን እያሉ መብታቸውን ለማስከበርና በሥራቸውም ለመከበር ይሞክራሉ አዎ መብታቸውን ለማስከበር ቢጥሩ ያስመሰግናቸዋል እንጂ አያስነቅፋቸውም (አያስነውራቸውም)

ነገር ግን መብታቸውን ለማስከበር ሲሉ ብዙ ሲደክሙ ከእነሱም የሚፈለግ አንድ ዓቢይ ነገር አለ፦ ይኸውም ግዴታቸውን ማሟላት በኃላፊነት የሚጠየቁበትን ሥራ በንቃትና በትጋት ሰዓትን አክብሮ መሥራት ነው ። ግዴታቸውን ካሟሉ በኋላ ግን መብታችን ይከበርን ቢሉ መልክ አለው ለሰሚውም ግራ ሊሆንበት አይችልም ፣ አንድ ሰው ወደ መሥሪያ ቤቱ በተወሰነ ሰዓት እየገባ የተመደበበትን ሥራ በሚገባ ከሠራና የሚፈለግበትን ሁሉ ፈጽሞ ከተገኘ ቢናገር ተደማጭነት ፣ ቢያመለክት ጉዳዩን ተቀባይነት እንደሚያገኝ የታወቀ ነው

ሥራቸውን ሳያከናውኑ ግዴታቸውን ሳያሟሉ መብታችን መብታችን የሚሉ ሰዎች ቢኖሩ ግን ተሳስተዋል ።

ለምሳሌ ባጭሩ ልንገነዘበው የሚገባ ነገር ጉልህ ሁኖ የሚታይ አለ በየአውራ ጐዳናው ከዚህ ቦታ መሽናት ክልክል ነው በማለት ማዘጋጃ ቤቱ ቀበሌውም ማስታወቂያውን ይለጥፋል ያስከብራል ነገር ግን ከተለጠፈው ማስታወቂያ ሥር ቁመው ሲሸኑ ይገኙና የጽዳት ሹም ለምን ከዚህ ትሸናላችሁ ሲላቸው መብታችን ነው ብለው የሚመልሱ ጥቂቶች አይደሉም ፣ ግን ከመብታቸው አስቀድመው ግዴታቸውን ማወቅ ነበረባቸው ።

ይህም ይህ ነው ከዚህም ሌላ አንዳንድ ሰዎች ለሰው ልጅ ከተወሰነለት በላይ ጠጥተው ከሥካራቸው ብዛት የተነሣ በየመንገዱና በየአውራ ጐዳናው ትልቁንና ትንሹን በጠቅላላ አፋቸው እንአመጣላቸው አሳፋሪ ነገርን ሲናገሩ ለምን እንዲህ ትሆናላችሁ ሲሏቸው የፈለግነውን ብንናገር መብታችን ነው በመብታችን የሚገባብን የለም ሲሉ ይመልሳሉ ።

እንግዲህ እነዚህ ሰዎች መብት የሚለው ንባቡ እንጂ ትርጉሙ የገባቸው አይመስለኝም የመብት ትርጉም ቢገባቸውስ ከእነሱ የሚጠበቅ ግዴታንም ባወቁ ነበር ትርጉሙንና ምሥጢሩን ካለማወቃቸው የተነሳ ግን መብት በሚለው ቃል ብቻ ለመጠቀም ይሞክራሉ

ወደ ገጽ ፳፰ ዞሯል

---

ቻሉ? አጠያያቂ ሆኖ የተገኘውም ይኸው ቃል ነው ጠለቅ ብለን ስንመረምረው ግን ከወጣቶች የተለያዩ ምክንያቶች እናገኛለን ።

“የማኅበራዊ ኑሮ መሠረት የሆነውን ቅዱስ ጋብቻ የምንሸሸው ይላሉ ወጣቶች በገንዘብ ፣ በቁንጅና ፣ በጠባይ ፣ በትምህርት ከፍተኛውን ደረጃ ይዘው የሚገኙ እንዲሆኑ እንመኛለን ለጋብቻ መሰናክል ከሆኑን አንደኛው ምክንያት ይህ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ድንገት መጋባት ቢመጣ በኑሮ መቸገር ፣ በጤና መታወክ በአጠቃላይ ከመዝናናት ተወግደን ወደ ወጥመድ ውስጥ መግባት ይመጣል ብለን በማሰብ ነው ” የሚል አሳብ ያቀርባሉ ።

ወጣቶች ጋብቻን ከፈሩበት ዋናው ምክንያት ገንዘብ ቁንጅና ጠባይ ያላትን ወይም ያለውን አለማግኘታቸው ነው ብለዋል ይህን ጥያቄ ለማሟላት እጅግ አስቸጋሪ ሆኖ መገኘቱን ያልመረመሩ ይመስላል ምክንያቱም በብዙ ቦታ ጋብቻን ሲመሠርቱ ለፈላጊው ሰው (አማጭ) የሚያቀርቡት ጥያቄ በጣም ቆንጆ የሆነች (የሆነ ) የተማረችና ሥራ ያላት (ያለው) በጠባይና በሥራ አቅዋም የታወቀች (የታወቀ) ይህን የመሳሰለው ነው ።

ስለዚህ ጥያቄ የሚሰጣቸው መልስ ደግሞ “እንዲህ ያለችው ከተገኘችስ እኔም ኣለቅ” የሚል ነው ወጣቶች ይህን በመሳሰለ ምክንያት ከጋብቻ ርቀዋል ። በዚህ ዓይነት ከቀጠሉ የያዙት ጉዳና የጥፋት መሆኑን ቢረዱልን እንወዳለን ።

ወጣቶቹ ትኩስ አእምሮ ሚዛናዊ አስተሳሰብ ያላቸው ናቸው ብለን እናስባለን ። ነገር ግን በዚህ ይዞታቸው የጋብቻን ሁኔታ በሚዛናዊም ርምር ተመልካቾች ሆነው አላገኘናቸውም ።

ወጣቶች ጋብቻን ለመመሥረት ከአስፈላጊው በላይ በገንዘብና በቁንጅና የተሟሉ እንዲሆኑ ሲጠየቁ የወላጆችም መንፈስ በዚህ ላይ ያተኮረ ይመስላል ይህ ከሆነ በዚህ ዓይነቱ አስተሳሰብ ከተመሠረተው ጋብቻ የሚገኘው ፍጥረት እግዚአብሔርን የሚፈራ ፣ ቤተሰብን የሚያከብርና አገርን የሚወድ እንደማይሆን እናምናለን ይህንኑም ወጣቶች እንዲያውቁልን ይህንን መልእክት እናስተላልፋለን ።

እንግዲህ በአጠቃላይ ስለተጋቢዎቹ ቤተክርስቲያን የምትሰጠው ምክር ቢኖር ከላይ በወጣቶች ምኞት እንደተገለጸው ሴትዋም ሆነች ወንዱ በጥያቄው መሠረት አሟልተው ቢገኙ አሳቡ የሚደገፍ ነዉ ።

ነገር ግን ከፍ ያለ ደመወዝ ያላት (ያለው) ትምህርት ከጠባይ ቁንጅና ከውበት ጋር ያላት(ያለው) እየተባለ በክርስቶስ የታዘዘ የቅዱስ ጋብቻን ጊዜ በከንቱ ማሳለፍ ተገቢ ሆኖ አናገኘውም ።

ወጣቶች አተኩረው ቢያስቡበት እነዚህ ሁሉ ከጋብቻ በኋላ በመመካከርና በመወያየት ፣ እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን አካል ማንም ሊለያየው እንደማይችል እምነት በመጣል መፍትሔ ሊገኝለት የሚችል ጉዳይ ነው ይህም አሳብ በተግባር እንዲገለጽ ካስፈለገ ከጋብቻ በፊት ወደ እግዚአብሔር ማመልከትና በጸሎት መጠየቅ ክርስቲያናዊ ግዴታና አስፈላጊም ነው ።

መልካም ሚስትም ሆነ መልካም ባል የሚገኘው በጸሎት ኃይል ነውና ለምሳሌ ይስሐቅ በአባቱ ፈቃድ እግዚአብሔርን በመለመን ባደረገው ጸሎት በጠባይም ሆነ በቁንጅና ርብቃን የመሰለች ሸጋ ሚስት አግኝቷል ።

በዘመናችንም ቢሆን አንዳንድ ክርስቲያን ወጣቶች በመጸለይና በማዘን የፈለግዋትን ሚስት በማግኘት መሠረት ያለው ጋብቻን መሥርተዋል ።

ዛሬ በወጣቶች አካባቢ ያለውን አስተሳሰብ ስንመረምር ጋብቻን ለመመሥረት በረቀቀ ዘዴ ካልፈጸሙት ማንኛውም አቀራረብ የሚያስደስታቸው አይሆንም ።

እንግዲህ “በጠባያቸው የተበላሹ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች የምድር ገሃነም ናቸው” እንደተባለው ይህ እንዳያጋጥማችሁ በጸሎት እግዚአብሔርን እያሰባችሁና ጠቢቡ ሰሎሞን “ልባም ሴትን ያገኘ በረከትን አገኘ ከእግዚአብሔር ዘንድ ፀጋን ይቀበላልና” እንዳለው ይህ እድል እንዲያጋጥማችሁ እንመኛለን ስለሆነም ለጋብቻ ቁንጅና ሀብትና ውበት በቂ ስላይደለ በዚህ ምክንያት የጋብቻ ጊዜአችሁን በከንቱ እንዳታጥፉ አስቡበት እንላለን ።

በለጠ አበበ



## የእመቤታችንን ሥዕለ ቅርፅ የያዘ የዛፍ ሥር ቸኮዝላቫኪያ



በቸኮዝላቫኪያ የተገኘው የእመቤታችን ሥዕለ ቅርፅ ።

በርእሱ ላይ የተመለከተውን ለማመን ግራ ያጋባ ይሆናል ነገሩ ግን ርግጥ ነው በአሁኑ ጊዜ በቼኮዝሎቫኪያ ውስጥ በዛፍ ሥር የሚገኙትን ጉቶዎች የሚመረምር አንድ ቡድን ተቋቁሞ ሥራውን ሲያካሂድ ከቆየ በኋላ አሁን ይህ ቡድን የፈጸማቸውን የሥራ ውጤት በተግባር ላይ በማዋል ተጨምሮ ያገኛቸውን ሥዕለ ቅርፆች የኤግዚቢሽን ባዛር ከፍቶ ለሕዝብ በማሳየት ላይ ይገኛል።

በአሁኑ ጊዜ ባዛሩ ለሕዝብ ያቀረባቸው ሥዕለ ቅርፆች ምንም የሰው ጥበብ ያልነካቸው በተፈጥሮ ብቻ ተውበው የተገኙ መሆናቸውንም የቼቲክ የወሬ ወኪል በአስተላለፈልን ዜና ለመረዳት ተችሏል። ባዛሩ በዚህ ዓይነት አደራጅቶ ያዘጋጀው ሥዕለ ቅርፆች 150 ልዩ ልዩ ቅርጾች የያዙ ለመሆናቸው ዜናው ጨምሮ ገል ጿል ከተገኙት ሥዕለ ቅርፆች መካከልየቅዱሳን የመላእክትና በተለይም የእመቤታችን ሥዕለ ቅርፅ ጎልቶ ተገኝቷል ከእነዚሁ ሥዕለ ቅርጾች መካከል ልዩ ልዩ አቀራረብ ያላቸው የሰው የአራዊት የእንስሳትና ሌሎችም ወዘተ ተገኝተዋል።

ነገር ግን በተለይ ከደረሱን ሥዕለ ቅርፆች ምሥል ከዛፍ ሥር ምንም የሰው ልጆች ጥበብ ያልነካው በተፈጥሮ ብቻ የተገኘ የእመቤታችን ሥዕል እጅግ በጣም የሚያስደንቅ በመሆኑ ሥዕሉን እንዳለ አውጥተነዋል።



www.ethiopianorthodox.org

የመጽሐፍ ቅዱስ ዓምድ

# ኢየሱስ ከሞት ተነሣ ፤

(ማቴ. 28 ፥ 1—10 ። ማር. 16 ፥ 1—8 ። ዮሐ. 20 ፥ 1—10 ።)

1. ሴቶቹ ያዘጋጁትን ሽቶ ይዘው እሑድ ጠዋት በማለዳ ወደ መቃብሩ ሄዱ ፤ 2. መቃብሩ የተዘጋበትን ድንጋይ ከመቃብሩ ወዲያ ተንከባሎ አገኙት ። 3. ወደ ውስጥ በገቡ ጊዜ ግን የጌታ ኢየሱስን አስክሬን አላገኙም ። 4. ስለዚህም ነገር በመገረም ላይ ሳሉ እነሆ የሚያንጸባርቅ ነጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች በድንገት መጥተው በአጠገባቸው ቆሙ ። 5. ሴቶቹም እጅግ ፈርተው ወደ መሬት አቀርቅረው ሳሉ ሰዎቹ እንዲህ አሉአቸው ፤ «ሕያው የሆነውን ኢየሱስን ከሙታን መካከል ስለምን ትፈልጉታላችሁ ? 6. እርሱ እዚህ የለም ፥ ተነሥቶአል ፥ በገሊላ በነበረበት ጊዜ የነገራችሁን አስታውሱ ፤

ሮሜ ፲፱፥፱-፲፫

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ።
☎ 122033 ✉ 30750
አዲስ አበባ

## መብት ከግዴታ ጋር

ከገጽ ፩፮ የዞረ

ይሁን እንጅ መብት ሊከበር የሚችለው ግዴታም ሲከበር ጭምር ነው መብት ከግዴታ ግዴታም ከመብት ተነጥለው አይታዩምና ነው ። አንድ ሠራተኛ ራሱ የሥራን ሰዓት እየሠረቀና የሚፈለግበትን ግዴታ ወደኋላ እየጐተተ በሐላፊነት የሚጠየቅበትንም ሥራ በቸልተኛነትና በግድየለሽነት የሚመለከት ከሆነ ግዴታውን ባለመፈጸሙና በሠረቀው የሥራ ሰዓት ቢቀጣ መብቴ ተነካ ብሎ ቢጮህ በሆነና ባልሆነውም ነገር የሰውን ስም ቢያጠፋ ተቀባይነት ያገኛል ብዬ እምነት አልጥልበትም ፤ ነገር ግን መብቴ አልተከበረም ነፃነቴንም ተገፈፍኩ ለማለት የሚቻለው ሲጠሩት አቤት ፤ ሲልኩት ወዴት እያለ ተገቢውን ትእዛዝ እየፈጸመ የድካሙን ዋጋ በሚያጣበት ጊዜ ነው እዎ መብትና ግዴታ ተያይዘው ጐን ለጐን የሚሄዱና የማይለያዩ መሠረታውያን ተግባሮች ናቸው ። አንዱ ከንዱ ከተለየ ሁሉም የሉም በየመሥሪያ ቤቱ የሥራ መቆጣጠሪያ መዝገብ ከመሥሪያ ቤቱ ደጃፍ ተዘርግቶ እንደሚያረፍድ የታወቀ ነው ይሁን እንጂ ያ የሥራ መቆጣጠሪያ መዝገብ ከመሥሪያ ቤቱ በር ተዘርግቶ የሚያረፍደው ለመታየት ሳይሆን ሠራተኛውን ለመቆጣጠር ወደ ሥራው በወቅቱ የገባውንና በተወሰነ ሰዓት ያልገባውን ሠራተኛ ለማሳወቅ መሆኑ እሙን ነው ።

ግን ሰዓቱን አክብሮ በዚያው በተወሰነው ሰዓት ፈርሞ ወደ ቢሮው የሚገባው ሠራተኛ ግዴታውን ስላሟላ ግዴታውንም መብቱንም አስከበረ ማለት ነው ። በዚያው በተወሰነ ሰዓት ያልገባ ሠራተኛ ግን ወደ ሥራው እንዳልገባና ግዴታውን እንዳልፈጸመ ያ የሥራ መቆጣጠሪያ መዝገብ ስለሚመሰክርበት መብቱን ራሱ በራሱ ገፈፈ ይባላል እንጂ ማንም ሰው መብቱን ገፈፈው ለማለት አይቻልም ።

አንድ ሰው እበላበታለሁ ፤ እጠጣበታለሁ ፤ እለብስበታለሁ ፤ በጠቅላላ በፈለግሁበት ጉዳይ እጠቀምበታለሁ ብሎ በሥራው እምኖበት በንቃትና በትጋት እስከሠራበት ድረስ ምንጊዜም ቢሆን መብቱ የተጠበቀ ነፃነቱም የተከበረ ነው ።

ስለዚህ ግዴታን መፈጸም መብትን የማስከበር ሚዛን ስለሆነ ሚዛኑን የማክበርና የማስተካከል ግዴታ ያለበት ራሱ ሠራተኛው መሆኑ ግልጽ ነው፤ በግዴታው ጉድለት ካለም ራሱ ሠራተኛው ሊፈርደው የሚችለው ነው ስለዚህ እያንዳንዱ ሠራተኛ የሚፈለግበትን ግዴታ ሳይፈጽም መብቱን ብቻ ለማስከበር ማሰብ የለበትም መብትና ግዴታ የተያያዙና የማይለያዩ ናቸውና ።

ከነፈ እርግብ ማርቆስ

፩፰

# ኢ.ኦ.ተ.ሐ.ድ

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፤ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፤ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፤ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት

ስልክ ቍ. 116616
የመል. ሣ. ቍ. 3137
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org